አጠቃላይ መጥፎ ምክር መካሪዎች፣ ሰዎች እውነትን እንዳይመሰክቱና ለሠሩት ሥራም ኃላፊነት አንዳይወስዱ የሰዎችን አእምሮ ከሚቆጣጠሩበት አንዱ ዘዴ ነው።

ለመሆኑ ሰዎች ከዚህ በላይ በሰድስት ነጥብ በዘረዘርናቸው ጉዳዮች ተገዥ የሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው? ሦስት መሠረታዊ ነገሮች አሉ።

1. የሰው ልጅ በባሕርዩ የማይሞት ስለሚመሰለው የያዘውን ነገር እንደያዘ ዘለዓለማዊ መሆን ስለሚፈልግ ነው፤
2. በዚህ ምድር ላይ የሰው ልጅ ሲኖር ሁል ጊዜ ደስታን ይፈልጋል፤ የያዘው ነገር ሰለማያረካው የሚያረካውን ነገር ለመፈለግ ከዚህ በላይ በዘረዘርናቸው ነገሮች ላይ ይጠመዳል፤
3. እኔነትንና የበላይነትን በዚህ ዓለም ላይ ለመገንባት ሁል ጊዜ የሰው ልጅ ይጥራል። ማንነትን የበላይ ለማድረግ የሚጥሩ ሰዎች በሙሉ ማንነታቸውን ያልተረዱ ናቸው።

በዓለም ላይ ስንኖር እግዚአብሔር የፈጠረን እያንዳንዳችን በእኔነታችን ስንቆምና ያ እኔነት ደግሞ እግዚአብሔር እሱነቱ በሕይወታችን ሲገልፅ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ በሰው የሕይወት ታሪክ ውስጥ ይህ ሁኔታ አልታየም። ሰው በሕይወቱ ሊኖረው የሚገባውን ነገር ለመኖር ዋሽቶ፣ ሳስቶ፣ አታሎና አጭበርብሮ ብቁነት ያገኘ ይመሰለዋል፤ ነገር ግን ያ በሰው ታሪክ ውስጥ ሲገኝና ሲሆን አይታይም። የአገራችንን የአሰተዳደርና የኅብረተሰብ ታሪክ ስንመለከተው ይህንኑ ህቅ ነው የሚያስረዳን።

ምርጫችን ምን ይሁን? የፈለግነውን ካላገኘንን፣ አግኝተንም ካልረካን፣ እንረካበታለን ያልነው ነገርም ዘለዓለማዊ ካልሆነ ምርጫችን ምን ይሆን? የሚቀጥለው ክፍል ስለዚህ ጉዳይ ያብራራል።

ክፍል ሦስት

ምርጫችን ምን ይሁን?

ይህ ርዕስ ሰው አዋቂ፣ አስተዋይ፣ ተመራማሪ፣ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ለይቶ የሚረዳ ስለሆነ ሕይወቱን የተሟላ አድርጎ ለመኖር በእውቀቱ ተጠቅሞ ምርጫውን ማስተካከል እንደሚኖርበት ያስተምራል። ሰው በሕይወቱ ሁል ጊዜ ደስተኛና የበላይ መሆን ይፈልጋል፤ እንከን አልባ ኑሮ ለመኖርም ይጥራል። በክፍል ሁለት ከ1 እስከ 6 በተዘረዘሩ ማብራሪያዎች ሰው የማይፈልገው ነገር አንድ ብቻ ነው።

እሱም የበታች ያደርገኛል የሚለውን ስሁተቱን መቀበል ነው። ከዚህ የተነሣ የበላይ ለመሆንና ቡተሠራው ሰህተት ላይ ተጠያቂ ላለመሆን ከእውነቱ ለማምለጥ ብዙ ምክንያቶች ደርድሯል፤ ይደረድራልም። ይሁን እንጂ ከላይ ያየናቸው ጉዳዮች የሚያስተምሩን፣ ሰው በሚያገኘው ሊረካ ያለመቻሉን ነው። ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ ተደርጎና ሆኖ ተጨንቆም ተጠቦም ሰው ከፈራው ነገር ሲያመልጥና እሆነዋለሁ ያለውን ሲሆን አላየነም።

በአንጻሩ ግን ባልፈሰገውና ባልጠበቀው መንገድ ሕይወቱ እየተዛባና ዓለም እየተመሰቃቀለ በመሄድ ላይ ነው።

የሰው ምኞትና ውጤቱ

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ነጥቦች የሚያመለክቱን፣ የሰውን እውነተኝነት ገጻ ባሕርይ ሳይሆን ሰው በውሸት ያልሆነውን ሆኖ ለመኖር ሲጥር ነው። ይህ ደግሞ ሰው እሱነቱን ሳይሆን መኖር በለማይችል በደስታ ፋንታ ኀዘንን፣ በፍቅር ፋንታ ጠብን፣ በማግኘት ፋንታ ማጣትን፣ በድፍረት ፋንታ ፍርሃትን ሲያይና ሲቀበል እንመለከታለን። ውሸት ሁል ጊዜ መራርና ክፉ ነገር ነው፤ ክፋት ካለ ደግሞ ደስታ የለም፤ ደስታ ከሌለ ደግሞ ኑሮ አስከፊና አስቀያሚ ነው። ስለዚህ ሰው ይህንን አስቀያሚ ሕይወት ለመለወጥና እንኩን አልባ ኑሮ ለመኖር ምን ማድረግ አለበት? ምርጫውስ ምንድን ነው?

በዚህ ጉዳይ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሊቃውንት ጥናት አደገኛ የሚል ቅጽል የተሰጠውን መጽሐፈ መክብብን የጻፈው ጸሐፊ ሕይወቱ እንዴት እንደነበር አብራርቷል። መጽሐፈ መክብብ የጸሐፊው ስም በግልፅ ባይታወቅም በምዕራፉ መጀመሪያና በመጀመሪያው ቁጥር በኢየሩሳሌም የነገሠ የሰባኪው የዳዊት ልጅ ቃል በሚል ራሱን ያስተዋውቃል። ይህ ጸሐፊ በእብራይስጥኛ ኮሄን የሚል ስም ተሰጥቶታል፤ በኛ ቋንቋ ካህን እንደማለት ነው፤ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን ሰባኪ ይለዋል።

ይህ ሰው በአካባቢው ከነበሩትና ከሚኖሩት ሰዎች በዕውቀቱና በምርምር ሥራው ከፍተኛ ቦታ እንደነበረው ይገልጻል። በዚሁ መጽሐፍ ላይ የተገለፀው ሰው ከባሕርዩ መለዋወጥ የተነሣ ራሱን መጽሐፉን በአንድ አረፍተ ነገር መግለፅ ያዳግታል። ጥበበኛው የሕይወትን አስመራሪነት ለመግለፅ አንዱን

አረፍተ ነገር ሳይጨርስ ወደ ሌላ አረፍተ ነገር ስለሚሄድ፣ የኑሮው ብልሃቱ እንዴት ምስቅልቅል እንዳለበት ይገልጻል፤ መጽሐፉ ከመጀመሪያው ምዕራፍ ሁለተኛ ቁጥር ላይ ራሱን ሰባኪ ብሎ ካስተዋወቀ በኋላ *"ከንቱ፣ ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል፤" (መክ. 1፣ 2)።*

በዚህ አረፍተ ነገር ላይ ይህ ሰው ምንም ዓይነት ተስፋ ያለው ነገር በዚህ ምድር ላይ አላገኘም፤ ከዚህ በፊት የነበረውን ነገር በሙሉ ወደኋላ መርምሮ ምንም ዓይነት መታሰቢያ እንደሌለው ተገንዝቧል። *ሰው በባሕርዩ ያለፈውን ነገር ለማስተወል ስለማይችል እንጂ በሱ ዘመን የሚደረገው ነገር ሁሉ ከሱ በፊት ባሉት ሰዎች ተደርጓል፤ ለተደረገው ነገር ግን ምንም መታሰቢያ የለውምና ፀሐይ ይገባል፤ ፀሐይ ይወጣል፤ ነፋስ ይነፍሳል፣ ዝናብ ይዘንባል፤ ሁሉም ሥራውን ይቀጥላል፤ የሰው ዓይን ይህን ሁሉ ዐይቶ አይጠግብም፤ ጆሮም ይህንን ሁሉ ሰምቶ አይረካም፤" (መክ. 1፣ 8)።*

ጥበበኛው ብዙ ተመራመርኩ ይላል፤ በኢየሩሳሌም ከነበሩት ሰዎች ይልቅ በጥበቡ ለመብለጥና ለመላቅ ምርምሩን ቀጥሏል። ፈለገ፣ መረመረ፣ የተሠራውን ነገር ሁሉ አየ፤ ያ ሁሉ ነገር ከንቱ ነው። በሱ ጥበብ ጠማማ ሊቀና አልቻለም፤ ጎደሎም ሊሞላ አልቻለም፤ *(መክ. 1፣ 18)።* ጥበበኛው ሌላ ነገር ትዝ አለው፤ ከዚያ በፊት ያልደረሰበት መሰሰውና ጥበብንና አብደትን ምንጫቸው ከየት እንደሆነ ለመረዳት ሞከረ።

እውቀት እየበዛ (እያደገ) ሲሄድ በዚያው ልክ ደግሞ መከራና ጭንቀት እየጨመረበት ሲሄድ *"በጥበብ መብዛት ትካዜ ይበዛልና እውቀትንም የሚጨምር ኀዘንን ይጨምራልና፤" (መክ. 1፣ 18)።* ጥበበኛው ከትምህርቱና ከእውቀቱ የተረዳው ብዙ ጉዳዮችን ነው። ለመዘርዘር አስቸጋሪ ቢሆንም በሃይማኖት ደረጃ ወደ እግዚአብሔር እየቀርብንና እግዚአብሔርን እያወቅን በሄድን ቁጥር ሁለት ነገር ይለማናል።

አንደኛ የእግዚአብሔር ታላቅነትና ግርማው፣ የእኛ ዝቅተኝነትና ወራዳነት ዳዊት እንደተናገረ *ለእኔ ትል ነኝ ሰው አይደለሁም* የሚለውን ልናስታውሰው ይገባልI *(ሊሳ. 6፣ 8)*። ሁለተኛ ኃላፊነት እየተሰማን የሰዎች መውደቅ፣ መንገላታት፣ መራብ፣ መጠማት፣ በዓለም ላይ ያለው የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚ፣ በአጠቃላይ የፍርድ መዛባት እየተሰማን ይሄዳል። ከዚህም የተነሣ ማወቃችንን እስከመጥላት እንደርሳለን። ለዚህ ነው ይህ ጥበበኛ እውቀት ጎዘንን የሚጨምር ትካዜን የሚያበዛ ነው የሚለው። ጥበበኛው ሥራውን ቀጠለI አሁንም ደስታ ለማግኘት እየጣረ ነው። ሁለተኛውም ምዕራፍ ልቤን ና በማለት ጠራሁት ብሎ ይጀምራል። ደስታን እንዲያጣጥም ይጋብዘዋልI ግን ያ ሁሉ ወዲያው ይጠፋና ከንቱ ይሆንበታል። ከዚያ እንደምንም ተረጋግቶ ወደ ኋላም ወደፊትም ተመልክቶ ራሱን በማረጋጋት በሕይወቱ ውሰጥ ለውጥ ለማምጣት አንድ ሥራ ይጀምራል።

በዚህ ሥራ ላይ በሕይወቱ ውሰጥ ታይቶ የማይታወቅ ለውጥ ለማምጣት የተጠቀመበት ዘዴ፣ በመጀመሪያ በሥልጣን የበላይነት በመጠቀም ብዙ ሴቶችን የወይን ጠጅ የሚጠመቅበትን የወይን እርሻ የሚኖርበትን፣ አካባቢ በአትክልት በውሀና በልምላሜ እንዲዋብ ያደርጋልI ታላላቅ ቤቶችን ይሠራልI ሙዚቀኞችና ዳንሰኞችን ያሰለጥናልI በጠቅላላ በአካባቢው አሉነቱን የሚያሳውቅ ነገር ይሠራል። ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ እንዲህ ይላልI *"ዐይኖቼንም ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኋቸውምI ልቤም ከደኻሙ ሁሉ ደስ ይለው ነበርና ልቤን ከደስታ ሁሉ አላራቅሁትምI ከድካሜም ሁሉ ይህ እድል ፈንታዬ ሆነI" (መክ. 2፣ 10)*።

ይህ ሰው ምንም ዓይነት ያጣው ነገር የለምI ሕይወትን እንኸን አልባ ለማድረግ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች ከሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ የተለዩ ናቸው። የሚያገለግሉት አገልጋዮች ሁሉ አሉትI በዚህ ሁሉ ደክሞ ግን ከንቱና ነፋሰን እንደመጨበጥ ሆነበት። ሰለዚህ ይህ ሰው አሁንም ልቡ በደስታ አልተሞላምና ሕይወቱ ዙሮ ዙሮ ከዚያ ጭንቅ አልወጣም።

ይህንን የጥበበኛውን ሕይወት በሁለት መሠረታዊ ነገሮች ላይ እናየዋለን። ይህንን ሁሉ አግኝቶ ሰውየው ካልተደሰተ በኑሮውም ለውጥ ካላመጣ ይህ ሰው የሚከተሉት ሁለት ነገሮች አጋጥመውታልI እነዚህም፣ ባዶነትና ብቸኝነት ናቸው።

ከላይ አንዳየነው ጥበበኛው እውቀት አለውI ገንዘብ ተርፎታልI ቤት አለውI በዚህ ዓለም የሚያስፈልገው የሴት ጓደኞች አሉትI ብቻ በሥጋ የፈለገው ነገር ተሟልቶለታልI ነገር ግን ደስታ የለም።

ሀሮልድ ኩሽነር "When All you're Ever Wanted Isn't Enough" በሚለው መጽሐፋቸው ውሰጥ በገጽ 16 በዓለም ላይ ሁለት አሳዛኝ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው አንድ ነገር ፈልጎ ማጣት ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ የፈለጉትን ማግኘት ይሉና ማብራሪያቸውን ይቀጥላሉ። ምንም ዓይነት ሥራ ጠንክረን እንሥራና የፈለግነውን ነገር እናገኛለንI ከአሰብነውም ግብ እንደርሳለን። በኋላ ግን ዞር ብለን ስናየው ያም አይበቃም። የዚህ ጥበበኛ ነገርም ይህንኑ ነገር ነው የሚያሰረዳን። ያለው ከመጠን ያለፈ ሥልጣንና ገንዘብ ዙሪያውን ያሉት አገልጋዮች ደስታ ያሰገኛሉ ተብለው በብዙ ገንዘብ የተቀጠሩ እውቅ ዘፋኞችና ዳንሰኞች ለዚህ ሰው ደስታ ሊሰጡ አልቻሉም። ሰው ኃይል በጨመረና ሀብት ባካበተ ቁጥር ከሰው እየተለየ የገንዘቡና የሥልጣኑ ጥገኛ ሲሆን የሰው ብቸኝነት እያጠቃው ይመጣል።

ፕሮፌሰር ጆን ሐዛወይ ስፔንሰር የተባሉት የኢትዮጵያ የሕግ አማካሪ የነበሩት "ETHIOPIA AT BAY" (ጥርሰ የገባች ሀገር) በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ያሰፈሩት ሃላብ ኢትዮጵያ በአፍሪካ የጦር ኃይል ብቸኛ የበላይ እየሆነች ስትመጣ ከአካባቢው እየተገለለች መሄዱን ይገልፃሉ። አጠቃላይ የጥንት መንግሥታትን ታሪክ ስንመለከት ባለሥልጣኖች ከሕዝብ ጋር የነበራቸውን ፍቅር እየተው፣ በኃይላቸውና በሥልጣናቸው እየተመኩ ሲሄዱ ብቸኛ ይሆናሉ። ያ ብቸኝነታቸው ደግሞ ንዴትንና የአእምሮ እለመረጋጋትን እየፈጠረ የኃይል እርምጃ በሕዝባቸው ላይ

እንዲወሰዱ ያደርጋቸዋልI መጨረሻ እንደዚህ ጥበበኛ ሥልጣናቸውም፣ ገንዘባቸውም ነፋስ እንደመጨበጥ ይሆናል።

በንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የነበሩት የፖለቲካ ሰዎች የንጉሠ ነገሥቱ ምንግሥት የእድሜው መጨረሻ ሲሆን የቻሰው፣ ባለሥልጣኖች ንጉሡን ጨምሮ እራሳቸውን ከሥልጣናቸውና በእጅ በሚዳሰስና በዐይን በሚታይ ንብረት ላይ በማድረጋቸው አወዳደቃቸው እንደከፋ ይናገራሉ። በቀድሞው ፕሬዚዳንት በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ቃለ መጠይቅ ሰም በተመሠረተ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘረው ሃሳብ ይህንኑ የኃይልና የሥልጣን የበላይነት ያመጣውን ብቸኝነት ያሰረዳል። እሳቸውም እንደሚሉት መጨረሻ ላይ ብቻቸውን እንደቀሩ ነው። በአንድ ወቅት ከስድሰት በላይ ማዕረግ የነበራቸው ሰው፣ በመጨረሻዋ ሰዓት ሁሉም ነፋስ እንደመጨበጥና ከንቱ ሆኖ ቀረ።

የደስታ ምንጭ

በመጽሐፈ መክብብ ላይ ራሱን የገለፀው ሰው ልምምዱ ይኸው ነበር። ሁሉም ነበረውI ጓደኛ ግን አልነበረውምI ዐይኑ ያየውን፣ ልቡ የፈቀደውን ማድረግ ይችል ነበርI ነገር ግን ሰው ሕይወት ባዶ ነበር። ስለዚህ ለዚህ ሰው ምርጫው ምን ይሆናል? ያ ሁሉ ድካም ለባዶነት ከሆነ፣ ያ ሁሉ ጥበብ ጎደሎና የማይሞላ ከሆነ ምን ይሆናል? ሕይወት ከንቱ፣ ነፋስ እንደመጨበጥ ነው።

በመጽሐፈ መክብብ ጸሐፌ ሕይወት ያየነው ሁሉ ነገር ተሟልቶ የፈለገውም ግብ ደርሶ ባዶና ነፋስ መጨበጥ ነው። ሀሮልድ ኩሽነር ከላይ በጠቀስነው መጽሐፋቸው ገጽ 17 ሰሰ አንድ ወጣት ምኞት ሃሳብና የደረሰበትን ይገልጻሉ። ይህ ወጣት ሦስት ነገሮችን ተመኝቶ ነበርI አንደኛው በትልቅ ስክሪን ላይ ስሙን እንዲያይI ሁለተኛው በውበት ተወዳድራ በዓለም ላይ 1ኛ ቆንጆ የሆነች ሴት ማግባት እንዲችልI ሦስተኛው በሆሊውድ የበላይነትን እንዲያገኝ። እነዚህ ሁሉ ሕልሞቹ ገና 30 ዓመት ሳይሞላው ተከናወኑI ያ ሲከናወንለት ግን በጭንቀት ውስጥ ገባ።

ጸሐፈው ሊያሰንዝሩ የፈለጉት ልክ እንደ ጥበበኛው ሰው የፈለገውን ባገኝ ቁጥር ከራሱና ከሌላው እየተለየ ሰለሚሄድ የጭንቀቱ ብዛት በዛው ልክ እየጨመረ ይሄዳል። ሚሮስላቭ ቮልፍ "Exclusion & Embrace" በሚለው መጽሐፋቸው በገጽ 14 ላይ "ሰው ያለ ለሌሎች ከኖረ ሕይወቱ ትርጉም ያጣል" ይላሉ።

በዘመናችን ብዙ እውቀትና ሀብት ያላቸው ሰዎች በብዛት ባካሄዳቸውI በአኗኗራቸው ከሰው እየተለዩ ይሄዳሉI ግማሾቹ ብዙ ገንዘብ ከማግኘታቸው የተነሣ ከአቅም በላይ የሆነ ቤት ያዘጋጃሉ። በአሜሪካ አገር የሚገኙ ተዋናዮችና ሃብታሞች የሚኖሩበት አካባቢ በይዘቱም፣ በጥራቱም ከሌላው የተለየ ነው። አካባቢያቸው በዘበኛ ይጠበቃልI የነሱም ሕይወት እንደዚሁ በጭንቀት ውስጥ ነው ያለው። ሌላው ቀርቶ ገንዘብ ከሚሠሩበት ሕዝብ እንኳን እጅግ ተለይተው ስለሚኖሩ ሕዝብ ስለነሱ ምን እንደሚል አያውቁምI አይረዱምI ይህ ደግሞ የውሰጥ ባዶነትን ይፈጥርና ያለ የሌለ ገንዘባቸውን ራሰን ለማስደሰት ያጠፋሉI ያም ደስታ አይሰጣቸውም። ልክ እንደጥበበኛው፣ ብዙ የአሜሪካ የፖለቲካ ተንታኞችና እውቀት ያላቸው ሰዎች የአሜሪካ የበላይነት ብቸኝነት ፈጥሮባታል ይላሉ። ይህ እውነታ በኢራቅ ጉዳይ ላይ በተነሣው ችግር ላይ ግልፅ ሆኖ ታይቷል።

አሜሪካ እበልጣችኋለሁ በምትላቸው በፈረንሳይና በጀርመን እንዴት እንደተቸገረችና አጣብቂኝ ውስጥ እንደገባች ተገንዝበናል። እንድ የአሜሪካ የሴኔተር አባል የሆኑ፣ ለአሜሪካ ከምንጊዜውም የበለጠ ሰው ያሰፈልጋታልI ድሀ የተባሉት አገሮች ለአሜሪካ አሰፈላጊ ሆነው ተግኝተዋል። ሰለሆነም ማንኛውንም አገር እንደ አገርነቱ መቀበልና ማክበር አሰፈላጊ ነው። ትልቅ ሊያሰኘን የሚችለውም ይሄው ተግባር ነው። አንድ የአፍሪካ ዲፕሎማት ሰለአገራቸው አቋም ተጠይቀው ሲመልሱ የኔ ቁልፍ ትንሽ ናትI ትልልቅ ቁልፍ ያላቸው አገሮች ትልልቅ ቁልፍ ከከፈቱ የእኔ የማታሰፈልግበት ጊዜ ሊመጣ ይችላልI ይሁን እንጂ ትልቅ ቁልፍ የማይከፍተው በር ካለ የትንሹ አሰፈላጊነትም የማይቀር ነው ብለዋል። በጠቅላላ ትልቆች ያለ ትንሾች፣

ትንሾችም ያለ ትልቆች ሊኖሩ አይችሉምI ጥበበኛው ይሆንን ሰላልተገዘበ ነበር ሁሉም ነፋስ እንደመጨበጥ የሆነበት።

የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ የሰውን ሕይወት ታሪክ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናልI የሰው ጭንቀት ምን እንደሆነ የወደፊት ዕድሉ ምን እንደሚመስል ይገልጻል። በዚህ ጸሐፊ ለሁሉም ነገር እጅግ አሰቸጋሪና አሰጨናቂ ሆኖ ያገኘው የሞትን አደገኛነት ነው። ብዙ ነገር አቅዶና አስቦ ለመሥራት በሁለት ምክንያት ደስታው ይሟጠጣል። አንደኛ ያ ሁሉ የደከመበት በሞት ጥሎት ከመሄዱም በላይ ሞት ራሱ ደግሞ እንደሱ ዓይነቱን ጥበበኛ ከሰነፉ ጋር እኩል በመውሰዱ ከባድና የሚያሳዝን ሊሸከሙትም የማይቻል ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ያንን የደከመበትን ሁሉ ለሌላ ሰው ጥሎት ማለፉ አሳዛኝ ነው። አባባሉ እንዲህ ተገልጿልI *"ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ሰው እተወዋለሁና ከፀሐይ በታች የደከምኩበትን ሁሉ ጠላሁት። ጠቢብ ወይም ሰነፍ እንዲሆን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? ከፀሐይ በታች በደከምኩበትና ጠቢብ በሆንኩበት ቢድካሜ ሁሉ ላይ ጌታ ይሆንበታልI ይህም ደግም ከንቱ ነው። እኔም ተመልሼ ልቤን ከፀሐይ በታች በደከምኩበት ድካም ሁሉ ተስፋ አስቆረጥሁትI"* *(መክ. 2I 18-20)*።

ይህ ሰው የሠራውና የደከመበት ሁሉ ለሌላ ሰው ማለፉ ብቻ ሳይሆን የሱ ተከታይ ሰው ማን እንደሆነ ሰላላወቀና ስላልተረዳ ሰነፍ ይሁን ወይም ጠቢብI ጨካኝ ይሁን ወይም ሩኅሩኅI ባለማወቁ ምክንያት የደከመበት ሁሉ ተሰፋ አስቆረጠው። ሥራውን እያሰበው በሄደ ቁጥር ጭንቀቱ እየጨመረ ሄደ። እሱ የሠራው ብቻ ሳይሆን የሰው ባሕርይና ተፈጥሮ ደክሞ ደክሞ ላልደከመI ሠርቶ ላልሠራና ከዚህ ግባ ለማይባልI የደከመበትን ሁሉ ያወርሳል። ይህ ደግሞ ከንቱI ትልቅ መካራም ነውI ይህም በሰው የሕይወት ዘመን ሁሉ ጭንቀትI ኃዘንI ፀፀትም ነው።

በጠቅላላ በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ ያየነው ሕይወት መራራና አሰቸጋሪ እንደሆነ ነው። ነገር ግን መጽሐፈ መክብብ ሰዎች ሊደሰቱበት የሚገባቸውን ነገር አንዳንድ የገለፃቸው ነገሮች

አሉ። መክብብ ሰው በሕይወቱ ደስ ሊለውና ሊያደርገው የሚገባው ነገር አንድ ነገር ብቻ ነውI እሱም በሠራው ሥራ ሁሉ መብላትI መጠጣትI እናም መደሰት ነው። *"ሰሰው ከሚበላና ከሚጠጣ በድካሙም ደስ ከሚለው በቀር የሚሻለው ነገር የለምI ይህም ደግሞ ከእግዚአብሔር እጅ እንደተሰጠ አየሁ። ያስ እርሱ ፈቃድ የበላ ደስ ብሎትም ተድላን የቀመሰ ማን ነው? እርሱም ደስ ለሚያሰኘው ሰው ጥበብንና እውቀትን ደስታንም ይሰጠዋልI"* *(መክ. 2I 24-26)*።

በዚህ ላይ ሁለት መሠረታዊ ነገሮች አይተናል። አንደኛ ሰው መደሰት የሚችሰው ከላቡ በሚወጣ የድካም ውጤትI በመብላትና በመጠጣት ያሰውንም በጥቅም ላይ በማዋል ሲሆንI ሁሰተኛው ደግሞ ይህ በሥራ የመደሰትI የመብላትና የመጠጣት ጉልበትና እውቀት ጥበብም የተገኘው ከእግዚአብሔር መሆኑን ነው። የዚህ ዓይነት ቃል ከጠቅላላው የመጽሐፉ አሥራ ሁለት ምዕራፎች ውሰጥI በሰድሰት ቦታዎች ከዘጠኝ ጊዜ በላይ ተጠቅሷልI ለምሳሌ፦

ምዕራፍ 2 ቁጥር 24I ምዕራፍ 3I ቁጥር 10-15I ምዕራፍ 3 ቁጥር 13-22I ምዕራፍ 3 ቁጥር 18-19I ምዕራፍ 7 ቁጥር 15-16I ምዕራፍ 9 ቁጥር 7-11።

እነዚህ ሁሉ ሰው በሥራውና በድካሙ መደሰት እንደሚችል ጥበበኛው የጠቆማቸው ሃሳቦች ናቸው። የሚያሳዝኑትም ደግሞ እጅግ በጣም ብዙ ሲሆኑI ከነዚህም ውሰጥ ሰው በአድሜው ሰብሰበ ወይም ሠርቶ ሳይጠቀምበት መሞት ነው። ሞት በአጠቃላይ ሲታይ ለሰባኪው እጅግ አሳዛኝና አስከፊ ነገር ነው። *መጽሐፈ መክብብ 2I 14-15I 2I 19I 3I 19I 6I 2-3* ባሉትና በሌሎችም ምዕራፎች የሞትን አሰቃቂነትና የሰው ልጅን ተሰፋ ቢሰነት አብራርቷል።

የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ በዓለም ላይ ምንም ዓይነት ቋሚና ዘሰቂታ የሚሰጥ ነገር የለም። ጸሐፊው መጽሐፉን ሁሉ ከንቱ ነው በሚል ጀምሮ የሚደመድመው ግን ምክር በመስጠት

ነው። የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ ሁሉም የሚጨበጠውና የሚዳሰሰው ነገር አስደንጋጭና አስፈሪ ከመሆኑ በፊት፤ ኃያላን የሚባሉትም ከመውደቃቸው በፊት፣ ሁሉም እንዳልሆነ ከመሆኑ በፊት ፈጣሪህን አስብ፤ ይልና ይህ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል። ሰባኪው ከንቱ፣ ሁሉ ከንቱ ነው ይልና መጽሐፉን የሚደመድመው እጅግ በጣም አዋቂ ስለሆነ እውቀቱን ለሕዝቡ አስተማሪ ፈላለገ፣ አስማማ፣ ሰባኪው ያማረውን በቅንም የተጻፈውን እውነተኛውን ቃል መርምሮ ለማግኘት ፈለገ ፤ *(መክ. 12፣ 9-10)*። በዚህ መጽሐፍ የምንረዳው አጠቃላይ ሰው ያስደስተኛል ብሎ የሚታመንበት ነገር ሁሉ በራሱ ደስታን የማይሰጥ በመሆኑ ሰው ምርጫው እንዳይሆን ጥበበኛው አስተምሯል።

ከላይ የጠቀስነው ቃል ሰባኪው ጠቢብ ስለሆነ እውቀትን ሁሉ ለሰዎች አስተማረ ይላል። ይህንን ሁሉ ካለና ሁሉም ከንቱ መሆኑን ካላየ በኋላ በአንድ አረፍተ ነገር መጽሐፉን ይዘጋል። *"የነገሩን ሁሉ ፍጻሜ እንሰማ ይህ የሰው ሁለንተናው ነውና፤ እግዚአብሔርን ፍራ፣ ትእዛዙንም ጠብቅ። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ፣ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን፣ ወደ ፍርድ ያመጣዋልና፤" (መክ. 12፣ 13-14)*።

ይህ አስደናቂ የሆነ ሰው፣ በሕይወቱ ሁሉ ደክሞ፣ ተመራምሮና ፈልጎ ለሰው ሕይወት ሁለንተና የሆነ ነገር ያገኘው እግዚአብሔርን መፍራትና ትእዛዙን መጠበቅ ነው፤ የእኛስ ምርጫችን ምን ይሆን?

ከዚህ በላይ ባየነው ሃሳብ መሠረት ትልቁና መሠረታዊው የሕይወት ማዕከላዊ ነጥብ እግዚአብሔር ነው። መጽሐፈ መክብብን ያነበበ ሰው የሕይወት ዋስትናን ለማግኘት መውጣት መውረድን፣ ሀብት ማካበትንና በዙሪያው በተጨባጭ ነገር መከበብን ወይም ተጨባጭ ነገር ለመደሰቻ ማዘጋጀትን ከንቱና ነፋስን እንደመጨበጥ ይሆንበታል። ጥበበኛው ያደረገው ጥረት ሁሉ ከሱ ከፊት በነበሩ ሰዎች ይበልጥ ነበር። ከአካባቢው ካሉትም ይልቅ ነበር፤ ነገር ግን

ሩጫውና ሙግቱ ከነፋስ ጋር ሆነና ነፋስ ደግሞ ስለማይጨበጥ ከንቱና የማይጠቅም ሆኗል።

ስለዚህ ከዚህ ሕይወቱ ለተከታዩ ትውልድ ጥበበኛው የሚያስተምረው ትምህርት አንድ ምክር ብቻ ነበር። እግዚአብሔርን ማመንና ትእዛዙን መጠበቅ፤ እግዚአብሔርን ፍራ ትእዛዙንም ጠብቅ የሰው ሁለንተናው ይህ ነውና። ለጥበበኛው እግዚአብሔር ሁሉንም ለፍርድ ያመጣዋል፤ *(መክ. 12፣13)*። ክፉም ሆነ በጎ በእግዚአብሔር ፊት ለፍርድ ይቀርባል። ስለዚህ ከዚህ ለመዳን ሰዎች የእግዚአብሔርን ምክር መስማትና ቃሉንም ማዳመጥ አለባቸው፤ ምክንያቱም ጥበበኛው ራሱ ወጥቶ ወርዶ የሕይወትን ደስታና ዋስትና እንዳላገኘ ሁሉ የሱ ቀጣይ ትውልድም ከዚህ ዓይነት ኑሮ ነፃ መውጣት አለበት።

መጽሐፈ ምሳሌ ይህንኑ በመደገፍ የሚከተለውን ይለናል። *"የአምላክንም እውቀት ታገኛለህ። እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣልና፤ ከአፉም እውቀትና ማስተዋል ይወጣሉ፣ እርሱ ለቅኖች ደህንነትን ያከማቻል፤ ያለነውር ለሚሄዱትም ጋሻ ነው፤" (ምሳ. 2፣ 6-7)*።

መጽሐፈ ምሳሌም የሚያስተምረን ይህንኑ የእግዚአብሔርን እውቀት ማወቅ ለሰው ልጅ አስፈላጊ እንደሆነና የእውቀትም ምንጭ ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣል፤ ከአፉም እውቀትና ማስተዋል ይወጣሉ፤ እውቀት ቢኖር ማስተዋል ከሌለ፣ ማስተዋል ቢኖር ደግሞ እውቀት ከሌለ ጎዶሰነት ነው። ከእግዚአብሔር የተማሩ ሰዎች ግን እውቀትና ማስተዋል አላቸው። እግዚአብሔር ራሱ በቅን መንገድ ለሚሄዱትና ቃሉን ለሚጠብቁት ጋሻቸው ነው፤ እግዚአብሔር ብቻውን ሠራተኛ ነው፤ ሥራም ቅንነትና እውነት ነው፤ ጥበበኛው ብቻውን ሲዋትት አጥቶት የነበረው ይህንኑ ነው። ሕይወቱ ባዶ ነበር፣ መንፈሱና አእምሮው የተረጋጋ አልነበረም፤ ስለዚህ ነበር ተከታዮቹን ወደ እግዚአብሔር ያመለከታቸው።

መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ሰው እግዚአብሔር ሠራተኛ እንደሆነና የድሆቹንና የተበደሉትን ጩኸት የሚያዳምጥ መሆኑን ያረጋግጣል። የእሥራኤልን ታሪክ ያጠና ሰው በባርነታቸው ጊዜ እንዴት እንደነበሩ፣ የ40 ዓመት የምድረ በዳ ጉዞ እንዴት እንደተጓዙ ማረጋገጥ ይቻላል። በዚያ ዙሪያቸውን በጠላት በተከበቡበት ጊዜ ከላይ ደመና ከታች እርጥበት ባልነበረበት ጊዜ ዙሪያውን የተቃጠለ አየርና በነፋስ የሚነዳ አቧራ በሚታይበት ጊዜ ሁሉም ነገር ተስፋ አስቆራጭ በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር ጠባቂያቸው ነበር። *(ዘፀአ. 14፣ 15-18፣ ዘዳ. 26፣ 6-11)* ይህንን እውነት ያረጋግጣል።

"ግብፃውያን ክፉ ነገር አደረጉብን፣ አሰጨነቁንም፣ በላያችንም ጽኑ ከባድ ሥራ ጫኑብን፣ ወደ አባቶቻችንም አምላክ ወደ እግዚአብሔር ጮህን እግዚአብሔርም ድምፃችንን ሰማ፣ ጭንቀታችንንም፣ ድካማችንንም፣ ግፋችንንም አየ። አግዚአብሔርም በጸናች እጅና በተዘረጋ ክንድ በታላቅም ድንጋጤ በተአምራትም በድንቅም ከግብፅ አወጣን፣ ወደዚያም ሥፍራ አገባን፣ ወተትና ማር የምታፈሰሰውን ይህችን ምድር ሰጠን፣" (ዘዳም. 26፣ 6-9)። አስገራሚ የሆነው ይህ ቃል እግዚአብሔር የድሆችን ድምፃቸውን መስማት ብቻ ላይሆን በሰው ልጅ ያለውን ሁለንተናዊ ድካም ተመለከተ። ድካማቸውን ዐይቶ ብርታትን ሰጣቸው፣ ጭንቀታቸውን ዐይቶ መጽናናትን ሰጣቸው። ጩኸታቸውን ሰምቶ እውነተኛ ፍርድ አደረገላቸው። እግዚአብሔር ሲፈርድ የሰው ጥበብ ሁሉ ከንቱ ይሆናል። አስፈሪና አስደንጋጭ የነበረው የፈርያን ኃይል እንዳልነበረ ሲሆን የሉም የተባሉት እሥራኤላውያን ኃይል ግን እንደ ብረት በረታ።

ጥበበኛው የተናገረው ይህንን ነው፣ ሁሉም በእግዚአብሔር ፊት እኩል ፍርድ ያገኛል፣ እሥራኤላውያን ያለ ኃይላቸውን በዚያን ጊዜ ቢጠቀሙ ኖሮ የመውጣት ተስፋ አልነበራቸውም። ታዲያ እንዲህ ላደረገ ጌታ መገዛትና ቃሉንም ማዳመጥ ታላቅ በረከት ነው፣ የሚለው ጥበበኛው። የዘዳግም ትምህርት በዚህ አያበቃም፣ አሁንም በሌላኛው ምዕራፍ እንዲህ ያላል፣ *"ዛሬም*

ያዘዝሁህን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ሰምተህ ብትጠብቅ ብታደርጋትም፣ ዛሬም ካዘዝሁህ ከእነዚህ ቃሎች ወደ ቀኝ ወደ ግራም ፈቀቅ ባትል፣ ታመልክባቸውም ዘንድ ሌሎችን አማልክት ባትከተል፣ እግዚአብሔር ራስ ያደርግሃል እንጅ ጅራት አያደርግህም፣ ሁል ጊዜ በላይ እንጅ በታች አትሆንም፣" (ዘዳ. 28፣ 13-14)።

ተቀዳሚ ምርጫ

ሰው በሕይወቱ ከሚፈልገው የመጀመሪያው ነገር ከአካባቢው ሁሉ በላይ መሆን ነው። ጠቅላላ ዓለማችን የውድድር ዓለም ስለሆነ ባለው አቅም ሁሉ ተወዳድሮ ከተወዳዳሪው በላይ ለመሆን ምኞትም ፍላጎትም አለ። የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊም ያደረገው ይህንኑ ነው፣ በሱና በዙሪያው ባሉት ነገሮች በፊትም ሆነ በኋላ ካሉት ተወዳዳሪዎቹ በልጦ መገኘት ነበር። እንዳለመታደል ሆነና ከንቱና ነፋስ እንደመጨበጥ ሆነበት። ከዚያ ተመልሶ ነው እንግዲህ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸምና እሱን መከተል በሱ ፈቃድ መሆን የሰው ሁለንተናው ነው ያለው።

ዘዳግም አሁንም የሚነግረን ይህንኑ ነው፣ የበላይ የመሆን አድል አለ፣ ከዚያ በፊት ግን የእግዚአብሔርን ቃል ማዳመጥና ትእዛዙን መጠበቅ ግዴታ ነው። ይህንን ግን አጠቃላይ በዓለምና በሥጋ የሚኖር ሕዝብ የተረዳው አይመስልም። በተለይም በሃያኛውና በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ የሚኖሩ የምዕራቡ ዓለም ምሁራን ሰለው ሕይወትና ሰኑሮ ዋስትና ትርጉም ለማግኘት የተጠቀሙበት ዘዴ አሁን ካልነው የተለየ ነው። ሎዊስ ኤል ሔይ የተባሉት ደራሲ "You Can Heal Your Life" በሚለው መጽሐፋቸው በገጽ 17 ላይ ሰው ለሕይወቱ ዋስትና ለማግኘት የደስታም ኑሮ ለመፍጠር ራሱ ይችላል፣ የመጀመሪያው መለኪያ የሕይወት ዋስትና ለማግኘት ራስን መውደድ ነው። ምንም ይሁን ምን፣ ምንም ይደረግ ምን የሰው ልጅ ችግር የሚመጣው እራስን

ካለመውደድ ነው፤ ራሱን የሚወድ ሰው ልክ ተአምራት እንደሚደረግለት ሰው ሕይወቱ የዚያን ያህል ይለወጣል።

ጸሐፊዋ ሲቀጥሉ የሕይወትን ሂደት ማዳመጥ፣ በመኖር መደሰት፣ ባየሁት ውብ ነገር መደሰት፣ ባየሁት ሌላ ሰው መደሰት፣ በዕውቀት መደሰት፣ በአእምሮ ዕውቀት መደሰት፣ በሰውነታችን አፈጣጠርና አኳኋን መደሰት፣ በባሕርና በየብስ ባሉት ፍጥረታት መደሰት፣ በቅጠላ ቅጠሎችና በፍሬዎቹ መደሰት፣ በጠቅላላ በዓለምና በተፈጥሮዋ መደሰት ይሉና ከዚህ ሌላ ምን መጨመር ያሰፈልጋል ይላሉ።

ጸሐፊዋ ከዚህ ያሰቀመጡትን የኑሮ ዋስትና መለኪያ ከዛሬ ሦስት ሺህ ዓመት በፊት መጽሐፈ መክብብን የጻፈው ጥበበኛው አሰቀምጦት ነበር፤ ጥበበኛውም እንደነዚህ ሊቅ በዕውቀት መደሰት፣ በሙዚቃ መደሰት፣ በዛፎችና በፍሬዎች መደሰት፣ በጠቅላላ በሠሩት ሥራ ሁሉ መደሰት፣ ታዲያ ያ ሁሉ የሆነበት ከንቱና ነፋስ እንደመጨበጥ ሆኖ ነው የቀረው። ለምንድን ነው እነዚህ ነገሮች ላያስደስቱ የሚችሉበት ምክንያት? የዘመኑ የሥነ ልቦና ምሁራን እንደሚሉት ሰው ሁሉን ነገር ካገኘና በራሱ ከተደሰተ የኑሮና የሕይወት ዋስትና ያገኛል ይላሉ። ነገር ግን የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ እንዳሳየን እነዚህ በሥጋዊ መንገድ ለመደሰቻ የተመረጡት ዘዴዎች ሁሉ በየደረጃቸው ዋጋን ይጠይቃሉ፤ በጸሐፊዋ በሔይ ግንዛቤ መሠረት ከተስማማን፣ ከላይ የዘረዘርናቸውን መለኪያዎች ለማግኘት ሰው በግድ ዋጋ መክፈል አለበት። ማለትም የጊዜ፣ የገንዘብ፣ የጉልበት ዋጋ መክፈል አለበት። ዋጋ የተከፈለበት ነገር ደግሞ ግዢ እንጂ ነፃ የልብ ደስታን ሊሰጥ አይችልም። ስለዚህ የሥጋዊ ነገር ሁል ጊዜ ከሥጋ ጋር የተያያዘ ስለሆነ መንፈስንና አእምሮን ሊለውጥ አልቻለም። ጥበበኛውም ቢሆን የተናገረው ይህንኑ ነው። ዳንሰኞቹን፣ ሙዚቀኞቹን ለመቅጠር ብዙ ገንዘብ አውጥቷል፤ የቤቱን ዙሪያ ለማስዋብ፣ መዋኛ ቦታዎቹን ለማሠራት ብዙ ገንዘብ አውጥቷል፤ ያ ሁሉ ግን ተስፋ አስቆራጭ ነው የሆነበት።

በምንኖርበት በአሜሪካን ጠንካራ ሠራተኞች ተብለው ከሚገመቱት የአሜሪካን ዜጋዎችና ነዋሪዎች ውስጥ እብዛኞቹ ከሚሠሩት የደመወዝ መጠን ምን አልባትም ሲሦውን እጅ የሚያስቀምጡት በዓመት ውስጥ በሚወስዱት የዕረፍት ጊዜ ለመደሰት ነው። የአሜሪካን የበጋው ዘመን ብዙው ሕዝብ ዕረፍት የሚወስድበት ነው። ከዚህም የተነሣ በምንኖርበት በኒው ዮርክ ነዋሪው ወደ ሌላ አገር ሲሄድ የሌላው አገር ሰው ደግሞ ወደ ኒው ዮርክ ይመጣል። እንደ አጋጣሚ እኔ ወደ ዕረፍት ከሚሄዱትም ከዕረፍት ከሚመለሱትም ሰዎች ጋር እገናኛለሁ። በተለይ የዕረፍት ጊዜያቸው ሲያልፍ ደክመው ነው የሚመለሱት፤ የሚሆነው ነገር ያጠራቀሟትንና ለዚያች ጊዜ ያሏትን መጨረሳቸው ብቻ ነው፤ ደስታው ግን አሁንም ፍጹም አይደለም። ይህ ሊሆን የቻለው ሰው ከውስጡ ለውጥ ከሌለውና የመንፈሳዊ ብልፅግና ካላገኘ በቀር በሥጋ ዕረፍት ማግኘትና በዚያም ምክንያት የለውን ሕይወት የኑሮ ዋስትና ሊለውጥ አይችልም።

ከላይ እንደተባለው ዓለም የውድድር መስክ ነው፤ በዓለም ያሉ ተወዳዳሪዎች ለመክሰርም ለማሸነፍ ወይም ለመሸነፍ ይወዳደራሉ። በአሜሪካን አገር የሚወዳደሩ ፕሬዚዳንቶች ለመሸነፍም፣ ለማሸነፍም ገንዘብ ያወጣሉ፤ በእስፖርት ዓለምም ቢሆን አንድ ተወዳዳሪ ውድድር ውስጥ ለመግባት ብቻ ዋጋ ይከፍላል፤ ችሎታም ቢኖረው ለመወዳደር የሚያበቃውን መመዘኛ ካላለፈ ሊወዳደር አይችልም፤ ያ ሁሉ ሆኖ መቶዎች ተወዳድረው አሸናፊው አንድ ብቻ ነው።

ሀሮልድ ኩሽነር "Living A Life That Matters" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ይህንን ሃሳብ ያንጸባርቃሉ። የሥጋ ተወዳዳሪዎች ብዙዎች ናቸው፤ አሸናፊ ግን አንድ ነው፤ የመንፈስ ተወዳዳሪዎች ግን የበዙትን ያህል አሸናፊዎችም ብዙዎች ናቸው ይላሉ (ገጽ 23)። ይህ ሃሳብ ትክክለኛ ሃሳብ ነው። በመንፈሳዊ መንገድ የሚወዳደር ሰው ለመወዳደር የሚያወጣው የለም፤ ሰው መንፈሳዊ ሕይወቱን ለመለወጥ ወይም ራሱን በመንፈሳዊ ዕድገት ለማሳደግ

ሌላውን አይመለከትም፤ ግንኙነቱ በእሱና በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ይሆናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በጻፈውና ወደ ፊልጵስዩስ በተላከው መልዕክት የሚከተለውን ቃል እናነባለን፤ *"ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፣ ደግሜ እላለሁ፣ ደስ ይበላችሁ። ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ። ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ፣ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃልና"* *(ፊልጵ. 4፣ 4-6)*።

ከላይ እንዳየነው የደስታ ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ይህንን ደስታ ለማግኘት የምናደርጋቸው ተግባሮች ጸሎትና ምልጃ ናቸው፤ ከዚህ ውጭ ጭንቀት የእኛን ሕይወት ሊለውጥ አይችልም። በጸሎትና በምልጃ የሚያስጨንቁንን ነገሮች በእግዚአብሔር ፊት ስናፈስ በገንዘብም በዕረፍትም አጠቃላይ የእኛ በምንለው ነገር ሁሉ የማይተመን የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንን ይዳስሳል። በገንዘብ የተገዛ ነገር ሁሉ ሁል ጊዜ ያወጣነውን ውጭ ስለምንተምን የደስታችን ዋጋ ሊሆን አይችልም። የሕይወት ዋስትና በገንዘብና በሌሎች የኑሮ ዘዴዎች ሊገኝ አይችልም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የያዕቆብ ታሪክ ትልቅ ትምህርት ሊሆነን ይችላል። በአሪት ዘፍጥረት ታሪካቸው ከተመዘገቡት ሰዎች ውስጥ ያዕቆብ ትልቁን ቦታ ይዟል። ፓትርያርኮች እየተባሉ ከሚጠሩት የመጽሐፍ ቅዱስ አባቶች የያዕቆብ ታሪክ የተለየ ነው፤ ያዕቆብ ለወላጆቹ ከመንትያ ጋር የተወለደ ሲሆን የወንድሙን ብኩርና በምስር ወጥ የገዛ በእናቱ አማካኝነት አባቱን አታሎ ቡራኬውን የወሰደ፣ ከዚያም 14 ዓመት ለአንዲት ሚስት፣ ከዚያም 7 ዓመት ለገንዘብ በጠቅላላ 21 ዓመት በራሱ የሕይወትን ዋስትና ለማቅናት የታገለ ሰው ነበር።

ከዚህ ሁሉ ዘመን ያዕቆብ ምን አልባት ስለ እግዚአብሔር ያስበበት ቀን ትንሽ ሊሆን ይችላል። ከ21 ዓመት በኋላ ልጅ ወልዶ ገንዘብ አፍርቶ ወደ አገሩ ሲመለስ እንድ ነገር ትዝ አለው። ይህም አታሎት ብኩርናውን በምሥር ወጥ ገዝቶ የወሰደበት ወንድሙ እንደሚበቀለው ነው። ስለዚህ የእናቱን አገር ለቅቆ ወደ አባቱ አገርም ሳይዝ መሀል መንገድ መሸበት። ሁለትም ሚስቶቹን፣ ልጆቹን፣ ከብቶቹንና መንጋዎቹን እንዲጠብቁ የቀጠራቸውን ሰዎች በመሉ መደፊት ልኳል፤ እሱ ብቻውን እንዳለ ድቅድቅ ጨለማ ሆነ። በዚህ ጊዜ አንድ ያልታወቀ ሰው መጥቶ ትግል ገጠመው፤ ሌሊቱን በመሉ በትግል አደረ። ሲነጋ ታጋዩ ሰው የያዕቆብን ጭን መታው፤ ስለዚህ ያዕቆብ ደከመ።

አሁን ሊደክም የሚታገለውን ሰው ሳይባርከው እንዳይለቀው ጠየቀው። ያዘው። ያ እንግዳ በዙሪያ የያዕቆብን ስም ቀየረው፤ ስሙ እሥራኤል ተባለ፤ ሰውንም እግዚአብሔርንም ታግሎ አሸንፏል ማለት ነው። ከዚያ በኋላ የያዕቆብ ህይወት የተለየ ሆነ፤ ያዕቆብን የሚጠሉት ሁሉ መዓረቁ ሆኑ። የያዕቆብ ጥርየት ወንድሙ የነበረው ኤሳው ይባርከኛል ነበር፤ ሆኖም ኤሳው ለመሣደል ሳይሆን በክብር ሊቀበለው መጣ፤ *(ዘፍጥ. 34፣ 3-4)*።

ከዚያ በኋላ ያዕቆብ ዘፍጥኖ ተንከልን ሁሉ ተመ፤ ስሙ የተቀየረው ያዕቆብ እስኑቱ ከተቀየረ በኋላ ነው፤ በክርስትና ሕይወት ሰዎች ክርስትናን ከመፈጸማቸው በፊትና በኋላ አንድ አይደሉም፤ አይሆኑምም። መጀመሪያ የነበረው በዓለም ያለውና የዓለም አሰተሳሰብ ለኃጢአት ይሞትና ለእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ለሆነው መልካም ነገር ሕያው ይሆናል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ እንደተናገረው "ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንኖራለንና ልክ አንደዚሁ ሁሉ ያዕቆብ ለክፉት ሞቶ ለመልካም ሰውነት ሕያው ሆነ፤" (ሮሜ 6፣ 1-6)።

በዓለምም እንደዚህ ነው፤ ሰው ራሱን ሳይለውጥና የውስጥ መንፈሳዊ ለውጥ ሳይኖረው የፈለገ ገንዘብ ቢያመጣ፣ የፈለገ በለማረ ቤት ቢኖር ሕይወቱ ጣዕም ሊያገኝ አይችልም።

ኢትዮጵያውያን ብዙ ጊዜ በእስፖርቱ ዓለም በሩጫ ያሸንፋሉ፤ ኢትዮጵያውያን ባሸነፉ ጊዜ ከአገር ውስጥ ያለው፣ በውጭም ያለው እልል ይላል፤ የደስታውም ተካፋይ ይሆናል። ባለፈው የሲድኒ ኦሎምፒክ ተወዳዳሪዎች የነበሩት 6 ኢትዮጵያውያን ሜዳሊያ ይዘው ኢትዮጵያ ሲገቡ ሞያ ያለው ሁሉ በዘፈን፣ በግጥም፣ በሽለላ፣ እንዲሁም የመንግሥት ባለሥልጥኖች በአበባና በእልልታ ተቀበሏቸው። ሁሉም ሰው ደስተኛ ነበር፤ ሁሉም ሰው እልል ይላል፤ ሁሉም ሰው ያጨበጭባል፤ ነገር ግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሜዳልያ አልተቀበለም። ሜዳልያ የነበራቸው ተወዳድረው ያሸነፉት ብቻ ናቸው። የዓለም ነገር እንደዚህ ነው፤ የደስታው ነገር የተወሰነ ሰለሆነ የሚያገኙትም ሰዎች የተወሰኑ ብቻ ናቸው።

የመንፈሳዊ ውድድርና አሸናፊዎች ግን ከላይ እንደተባለው ሰጭው ባለፀጋ ሰለሆነ ለእያንዳንዱም ተወዳዳሪ ባሸነፈ ጊዜ የሽልማት ዕድል ሰለሚያገኝ ከዚህ የተለየ ነው። ለዚህ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ *"መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ እሩጫየን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖቴን ጠብቄያለሁ፣ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል። ይህንንም ጽድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፤ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም"* (2ኛ ጢሞ. 4፣ 6-7)። የመንፈስ ተወዳዳሪዎች ሁሉም ሽልማትን እንደሚያገኙ ነው የሚያስረዳን።

በሥጋ መለኪያ ቢሆን ኖሮ ከሐዋርያው ጳውሎስ ሌላ በዚህ ምድር ላይ ሽልማት ሊያገኝ የሚችል የለም። ምክያቱም የሱን ያህል የሠራ የለምና። ጳውሎስ የሚያውቀው እግዚአብሔር ግን እንደ ጳውሎስ አባባል ከሆነ ለሮጡ ብቻ ሳይሆን መገለፁን ለሚፈልጉ ሁሉ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶላቸዋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ደቀመዛሙርቱ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ምን እናገኛለን? ብለው ሲጠይቁት፤ *"ለእኔና ለወንጌል ራሱን የሰጠ፣ አባቱንና እናቱን እህቱን የተወ ሁሉ፣ በዚህ ዓለም መቶ እጥፍ፣ በወዲያኛው ዓለም ደግሞ የእግዚአብሔርን*

መንግሥት ያገኛል ይላል" (ማር. 10፣ 29-30)። ይህ የሚያሳየው የመንፈስ ብልፅግና ወይም በመንፈሳዊ ዕድገት ማደግ ማትረፍ እንጂ መክሰር የሌለ መሆኑን ነው።

የምዕራቡ አገር ብልፅግና የሥጋ ብልፅግና ሰለሆነ ዓለምን የተፈለገውን ያህል ሊለውጥ አልቻለም። የሥጋ ብልፅግና ምን አልባትም ብዙ ሕንፃዎችን፣ ምን አልባትም የኢኮኖሚ አውታሮችን፣ የመገናኛ ዘዴዎችን ሊገነባ ይችላል። በዓለም ላይ ዛሬ የሚታየው ይህ ነው። የዓለም የመገናኛ ዘዴ በጣም ከመቀልጠፉ የተነሣ ከአንዱ አገር ወደሌላው አገር ለመሄድ እጅግ በጣም ቅርብ ነው። የኤሌክትሮኒክ መገናኛን ስንመለከት ከመቀልጠፉ የተነሣ በአንድ ጊዜ ብዙዎችን ከማስተናገዱም በላይ ቅልጥፍናውም የዚያን ያህል ነው። በተቃራኒው ግን የሰውን መንፈሳዊ ሕይወት መለወጥ ስላልቻለ የሰው አስተሳሰብ ከምንጊዜውም በላይ እየተለያየ መጥቷል። ይህ የሚያሳየው የሥጋ ብልፅግና የሰውን መንፈሳዊ ሕይወት መለወጥ አለመቻሉን ነው።

የመጀመሪያውን እ. ኤ. አ. በ1966 ዓ. ም. የተደረገውን የህገራችንን የለውጥ ሂደት ስንመለከተው ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው። የተካሄደው ለውጥ መንግሥት በመለወጥ ፋንታ የሰውን አእምሮ በመንፈሳዊ መልኩ ቢለውጥ ኖሮ ምን አልባት አሁን ከተደረሰበት የውድቀት ደረጃ አይደርሰም ነበር። መጀመሪያ የለውጥ ፈላጊዎቹ ለውጥ ብለው የተነሡት ሥልጣንን ከሰዎች ወደ ሰዎች መቀየር እንጂ፣ የራሰን ውስጣዊ ማንነትና ራሰ ወዳድነት ማሻሻልና መቀየር ስላልተቻለ እነዚያ ያደረጉትን የተሣሣተ ሥራ ተቃዋሚዎቹም አደረጉት። ከዚህ የተነሣ የሰው አእምሮ የሚያስተካክለውን ሃይማኖትን እንደትልቅ ጠላት በመቁጠር ከመለወጥ ይልቅ ሰውን የሚያደነዝዝ ነው በሚል ፍልሰፍና ተቃወሙት።

ከዚህም የተነሣ ከማደግ ይልቅ ወደ እርስ በርስ መገዳደልና ይህ ቀረህ ወደማይባል ጥላቻ ተጉዞ ከታሰበው መሻሻል ላይደረስ ቀረ። የአሁኖቹም ከዚያው ስህተት ላይ ስለተነሡ በምንም ዓይነት

የመሻሻል መንገድ አይታይም። አማኙ ከአማኙ ጋር፣ ባለሥልጣኑ ከበታች ሠራተኞቹ ጋር፣ ሕዝቡ ከሕዝብ ጋር ብቻ አንዱ ከአንዱ መረዳዳት ሲቻል መጠላላትና መለያየት ሆኗል። ምክንያቱም ሊቀድም የሚገባውን ነገር ማስቀደም ስላልተቻለ ነው።

ምርጫን ማስተካከል

ሰው በተፈጥሮው ሥጋና መንፈስ ስለሆነ ፣ ሥጋዊ ሕይወቱን ማታለል ቢችል እንኳን መንፈሳዊ አቋሙን ማታለል አይቻልም። መንፈሳዊ ነገር ተፈጥሮው ከእግዚአብሔር ስለሆነ መገቦትንና ትምህርትን የሚያገኘው ከራሱ ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። አግዚአብሔርን ያላስቀደሙ ሰዎችና በአምላካቸው ሥር ያልሆኑ ሰዎች ምን ቢበለጽጉ፣ ምን ቢጠበቡ፣ መጨረሻቸው ውድቀት ነው፤ አስካሁን በታሪክ እንደታየው ብዙ በሥጋዊ ጥበብ የበለጸጉ መንግሥታት ነበሩ፤ መጨረሻቸው ግን የሁሉም አላማረም። ሥጋዊ ነገር ለመፍረስ ምን አልባት አንድ ምሽት እንኳን አይጨርስም፤ በሥጋዊ ነገር አስፈሪነት የተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው ያለው። ደስታም እንደዚሁ የተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው ያለው። ስለዚህም ጥበበኛው እንዳለው መጨረሻው ከንቱና ነፋስ እንደመጨበጥ ስለሚሆን አሁኑኑ ረጋ ብሎ ማንነትን ማየት ያስፈልጋል።

በአንድ ወቅት የሀገራችን ርሃብ ተባብሶ የመንግሥት ወኪሎች የአካባቢውን ሕዝብ ስብሰባ ጠሩ። የስብሰባው ዓላማ የነበረው በአገር ውስጥ ለተቸገሩ ሰዎች የዕለት ምግብ ከኢትዮጵያውያኑ አስቸኳይ ዕርዳታ ማግኘት እንዲቻል ነበር። በስብሰባው ላይ ከተነሱት የመጀመሪያው ነጥብ ወጭ በዝቶብኛል፣ ገንዘብ አልሰጥም፣ ሳይሆን የምሰጠውን ገንዘብ ማን ለችግረኞች ያደርስልኛል ነበር። ምክንያቱም አገሪቱን የሚያስተዳድረው መንግሥት ታማኝ ስላልሆነ የሚሰበሰበውን ገንዘብ ለችግረኞች ሳይሆን ለግል ጥቅሙ ያውለዋል በሚል ሥጋት ነው። ይህ ምን ያህል አሳዛኝ ሁኔታ ነው። አንድ መንግሥት ሆኖ አገርን ይመራል

የተባለ አካል በዜጎቹ አልታመን ብሎ ገንዘብ አንሰጥህም ከመባሉም በላይ ራሱ ለሚያስተዳድራቸው ሕዝቦች ጭካኔን የሚያሳይ ነው።

የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ የሚመነጨው በቃኝ ከማይሉና እኔ ከሞትኩኝ ሰርዶ አይብቀል ከሚሉ ከማያምኑ ሰዎች ነው። የመጽሐፈ መክብብ ጸሐፊ መጀመሪያ ከማስተዋሉ በፊት የነበረው አስተሳሰብ የዚህ ዓይነት ነበር፤ መልካሙ ቤት ለእሱ፣ መልካሙ አካባቢ ለእሱ፣ ብቻ ጥሩ የሆነውን ነገር ለራሱ ማድረግ። ሲያስተውለው ግን ከንቱና ነፋስ እንደመጨበጥም ሆነ። ስለዚህም ሌላው ጥበበኛ እንደሚያስተምረው፣ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው። ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሳፅን ይንቃሉ። ስለዚህ የሀገራችን ችግር እንዲሁም በጠቅላላ የአኛ ዓይነት ችግር ያለባቸው ሕዝቦች ችግር የመጀመሪያ የበላይ ዳኛ፣ ሁሉን የሚያይ፣ የማይዳሰስ ነገር ግን የሚሰውረው የሌለ፣ ትንሹንም ትልቁንም በአኩልነት የሚያይ ሰማይንና ምድርን በውስጧ ያሉትን ሁሉ የፈጠረ አምላክ አለ ብሎ የሚያምን ሰው በሱም የሚገዛ ሰው ከዚህ ሁሉ ችግር ነፃ ይሆናል።

ዮሐንስ በራዕይው እንዲህ ይላል፤ *"ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል" (ራዕይ 4፣ 11)።* ናቡከደነፆርም ስለእግዚአብሔር ታላቅነት በተመሳሳይ ገልጸታል። *(ዳንኤ. 4፣ 35-36)።* ሰው ከእግዚአብሔር ያላገኘው ምን አለ? ከእግዚአብሔር ያልተቀበለው ነገር ምን አለ? ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ የሚመካበት ነገር ነበረው፤ የሮማዊ ዜጋ ነበር፣ በዘመኑ አሱም ያስመካ ክብር። የአይሁድ የሕግ ተማሪ ነበር፤ ይህም በዚያ ዘመን ለአይሁዶቹ ትልቅ ትምክህት ክብር። ይሄ ሁሉ ግን አላስመካውም፤ የተመካበት ነገር በተሰቀለው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር። በልቡ ደስታ ይሰማው የነበረውም ስለሱ ሲያስብና ሲሠራ ብቻ ነበር። ዛሬም እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ የሚያስመካን ነገር አለ። አገራችን ጥንታዊት ናት፤ የራሳችን ቋንቋ አለን፤ በሃይማኖትም፣ በተለይም ክርስትና ጥንታውያን ከተባሉት የክርስትና አገሮች አንዱ ኢትዮጵያ ናት። በማንም ቅኝ ገዥ

አልተገዛንም፣ የራሳችንን ማንነትና እኔነት የሚያሳይ ታሪክና ባሕል አለን። ነገር ግን ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ካልሆነ ከንቱና ነፋስ እንደመጨበጥ ነው የሚሆነው።

በጠቅላላ ሕይወትና የሕይወት ትርጉም ከእግዚአብሔር ውጭ ጣዕምና ዋጋ ሊኖረው አይችልም። በማጠቃለል በኦሪት ዘዳግም ያለውን ሃላብ እንመልከትና ይህን ሃላብ እንደመድመዋለን። *"እግዚአብሔር በረከቱ በአንተ ላይ በጎተራህ በእጅህም ሥራ ሁሉ እንዲወርድ ያዝሃልህ አምላክህ እግዚአብሔር በሚሰጥህ ምድር ይባርክሃል። የአምላክህን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ብትጠብቅ፣ በመንገዱም ብትሄድ እግዚአብሔር እንደማለልህ ለእርሱ የተቀደሰ ሕዝብ አድርጎ አቆምሃል። የምድር አሕዛብም ሁሉ የእግዚአብሔር ስም በአንተ ላይ እንደተጠራ አይተው ይፈሩሃልህ" (ዘዳግ. 28፣ 8-10)።*

ይህ የእግዚአብሔር ቃል የሚያሳየን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትና በሱ ስም የተጠሩት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ፈቀቅ ማለት እንደሌለባቸው ነው። በአካሄዳቸው፣ በአኗኗራቸው በጠቅላላ በነሱነታቸው እግዚአብሔርን ማሳየትና ማክበር መቻል አለባቸው። ያ ከሆነ በረከትን ያገኛሉ፣ የተትረፈረፈው የእግዚአብሔር ምህረት በነሱ ላይ ይሆናል፣ ካልሆነ ግን የሚከተለው ነገር ይደርስባቸዋል። *"ነፍስህም ታመነታለች ሌሊትና ቀንም ትፈራለህ፣ በሕይወትህም አትታመንም፣ አንተ ስለፈራህባት ስለልብህ ፍርሃት፣ በዐይንህም ስለምታየው አስተያየት ማለዳ መቼ ይመሻል? ትላለህ፣ ማታም መቼ ይነጋል? ትላለህ፣ ከአንግዲህ ወዲህ ተመልሰህ አታያትም። ባልሁህ መንገድም እግዚአብሔር በመርከብ ወደ ግብፅ ይመልስሃል፣ በዚያም ወንዶችና ሴቶች ባሮያዎች ትሆኑአቸው ዘንድ ለጠላቶቻችሁ ራሳችሁን ትሸጣላችሁ፣ የሚገዛችሁም አይገኝም።"* (ዘዳ. 28፣ 66-68)።

ይህ አስፈሪ ቃል እግዚአብሔር የመረጠን ሕዝቦች ነን ከሚሉትና ነገር ግን የተመረጡበትን ምክንያት ባልተረዱትና የሥጋዊ ጥቅምንና ብልፅግናን ለማግኘት በወንድሞቻቸውና

በእህቶቻቸው እሬሣ ላይ በሚረማመዱ አማጽያን ላይ የታወጀ የመከራ አዋጅ ነው። ምን አልባትም ዛሬ የሞላልን መስሎን በሚያብረቀርቁና ዙሪያቸውን አረንዴ በለበሱ ቦታዎች ብንኖር ነገ ያ ሲከዳን ከንቱና ነፋስ እንደመጨበጥ ሲሆንብን ግራ ከመጋባታችን በፊት አሁኑኑ ምርጫችንን እናስተካክል። ምርጫችን አንድ ብቻ ነው። እሱም በእግዚአብሔር በአምላካችን ጥላ ሥር ሆነን፣ እሱ የሚለንን ጆሮአችን እያዳመጠ፣ ታሪካችንን ወደ ኋላ ዞር ብለን እያነበብን፣ ስህተታችንን በእግዚአብሔር ቃል ሚዛን ላይ በማስቀመጥ እለት እለት እሱን መሻት ብቻ! ከዚያ ውጭ ፈውስ የለም።

ዛሬ የኢትዮጵያውያን ሕይወት በሚያሳዝን ሁኔታ የሚታየው በተፈጥሮ ተበድለን፣ በእውቀትም ከሌላው አንሰን፣ በማዕድንም ከሌላው ተራቁተን አይደለም። ችግራችን አንድ ብቻ ነው። እሱም የራስን አእምሮ ለውጠ ከሌላው ጋር አብሮ ለመሥራትና ለመደማመጥ ራስን ማዘጋጀት አለመቻል ነው። ለዚህ ደግሞ የሚረዳን እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ምርጫችን እግዚአብሔር ይሁን።

ክፍል አራት
የእግዚአብሔር የበላይነት በሕይወት ሚዛን ላይ

መጽሐፍ ቅዱስን ስንገልፅ በመጀመሪያው ምዕራፍና ቁጥር ላይ *"በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ"* የሚል ቃል እናገኛለን፤ *(ዘፍጥ. 1፣1)*። የሃይማኖታችን መግለጫ የሆነው ጸሎተ ሃይማኖት በመባል የሚታወቀው መግለጫችን ሁሉን በያዘ ሰማይና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በእግዚአብሔር እብ እናምናለን ይላል። እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ ሁለት ቃላት በክርስትና እምነት ለምንኖር ሰዎች የሃይማኖታችንና የሕይወታችን የመሠረት ድንጋይ፣ የኑሮአችንም የብረት ምሰሶ በመሆን ያገለግሉናል። ቃሎቹን በደንብ ስንመለከታቸው በዚህ ምድር ላይ የሚታይም፣ የማይታይም፣ ረቂቅም፣ ግዙፍም፣ ቅርብ ሆነ እሩቅ በእግዚአብሔር ጎልውናና አፈጣጠር ላይ የተመሠረተ ነው። ከዚህ የተነሣ ተፈጥሮ በሙሉ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነው ማለት ይቻላል።

እግዚአብሔር ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን ፍጥረታት በሙሉ በሥርዓት እንዲሄዱ መጋቢም ጠባቂም ነው። የዝናብ መዝነብ፣ የክረምትና የበጋ መፈራረቅ፣ የእንስሳትና የአራዊት በሥርዓት መሄድ፣ እግዚአብሔር የሕይወት ሚዛን የበላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። ዓለም ከተፈጠረና ወይም ሰው በዚህ ምድር መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ፣ ሰው በሰው ላይ ማድረግ የፈለገውን ማድረግ ቢችል ኖሮ የሰው ዘር እስካሁን ተላልቆ ባለቀ ነበር። ሆኖም ግን እግዚአብሔር የሕይወት ሚዛን የበላይ ስለሆነ ሰው የፈለገውን እንዳያደርግ የጎሊና ዳኝነት በመስጠት የዓለምን እንቅስቃሴ በበላይ ይቆጣጠራል።

በዓለም ያሉ ሰዎች ከዕውቀት ማነስ የተነሣ ለእግዚአብሔር የተለያየ ቅጽልና ስም ይሰጡታል። ከላይ የጠቀስነው የሃይማኖት መግለጫችን በሃይማኖት መግለጫና መመሪያነት እንዲወጣ ካደረገው ነገር አንዱ፣ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ዕውቀት ያላቸው አመለካከት የተለያየ በመሆኑና የእግዚአብሔር በማዳን ሥራ ላይ ያለውን የበላይነት ያለ አግባብ በመተርጐማቸው ምክንያት ነው። የግኖስቲክ ምሁራን፣ እግዚአብሔር ታላቅ ስለሆነ እርኩስና ዝቅተኛ ከሆነው ከሰው ጋር የማዳን ሥራውን ለማከናወን ከእግዚአብሔርነት ያነሰ ባሕርይ ያስፈልገዋል በማለት ነበር። ከዚህም የተነሣ ለዝቅተኛው ፍጡር ዝቅተኛ አምላክ፣ ለከፍተኛውና ለእዋቂው ምሁር ደግሞ ከፍተኛ እምላክ እንዳለው፣ በማመንና በመቁጠር ያስተምሩ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደነሱ ስለማያስተምር፣ የሚታዩትም ሆነ የማይታዩት፣ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ፍጥረታት ሁሉ በእግዚአብሔር እንደተፈጠሩና በእግዚአብሔርም እንደሚጠበቁ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወሰኑ፤ *ዘፍጥረት 1፡ 29-30* የሚያስተምረን ይህንኑ ሀቅ ነው።

እግዚአብሔር ትልቁንም ትንሹንም በእኩልነት ስለሚመለከት በኃይለኛው በፈርዖን ይገዙ የነበሩት እሥራኤላውያን ለፈርዖን ዐይን ትንሽ ቢመስሉም ለእግዚአብሔር ታላቆች ነበሩ። ስለዚህም በጽኑ መከራና በጽኑ ባርነትና በብርቱ ሥራም ያሰጨንቋቸው ዘንድ ኑሮና ሕይወት እስከሚመራቸው ድረስ ይጠበቡባቸው ዘንድ የረገጧቸውን እሥራኤልን እግዚአብሔር እርቆ በሚያዩ ዐይኖቹ ተመለከታቸው፤ *(ዘዘጸ. 1 ቁጥር 11-14)*።

ጥበበኞችና እስተዋዮች ነን የሚሉት እንደሚያስተምሩት በዓለም ውስጥ ከተፈጠረው ፍጥረት የእግዚአብሔር እጅ ያልነበረበት መልካም ያልሆነ እልነበረም። ሁሉም አስደናቂና የእማሬም ነበር። ሰው የሚበላው፣ የሚጠጣው፣ የሚደስትበትና የሚኖርበት እንዲኖረው ያም ደግሞ በሥርዓት መኖር እንዳለበት በእግዚአብሔር ተፈጥሯል፤ ተዘጋጅቷልም። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠረ፤ *በዘፍጥረት 1፣ 26* በማንኛውም ቦታና ጊዜ እርስ በርሱ ሊከባበርና እብሮ ሊኖር እንደሚገባም መጽሐፍ ቅዱስ

ያስተምረናልI እግዚአብሔርም የሚያዝዘው ይህንኑ ነው። ይህን ያልተረዱ፣ ከእግዚአብሔር ሥራ ጋር የሚቃረን ሥራ የሚሠሩት ግን የዚህ ሁሉ ተቃራኒ በመሆን እግዚአብሔርን የከፍተኛና የዝቅተኛ ፍጥረት ፈጣሪ ከማድረጋቸውም በላይ ራሳቸውን ከከፍተኞች በመቁጠር የእግዚአብሔርን ሃሳብ ሲቃወሙ ይኖራሉ። ንጉሥ ዳዊት ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት እንዲህ ይላል። *"አቤቱ በሰማይም በምድርም ያለው ሁሉ ያንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል ድልና ግርማ ለአንተ ነው። አቤቱ መንግሥት የአንተ ነውI አንተም ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያልክ ራስ ነህI" (1ኛ ዜና 29I 11)።*

በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የእሱ የሆነ፣ ነገሥታት ከነሥልጥናቸው፣ ሕዝቦች ከነ ንብረታቸው የሱ ብቻ የሆኑ እሱም የነሱ ራስ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ዳዊት ምስጋናውን ሲቀጥል *"ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነውI እንተም ሁሉን ትገዛለህ ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው።" (1ኛ ዜና 29I 12-13)።* ታላቅ ለማድረግ ለሁሉም ኃይልን ለመስጠት በእጅህ ነውI በዳዊት ትምህርት መሠረት ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ነውI ጥበብም፣ ማስተዋልም፣ ከእግዚአብሔር ነው። እያንዳንዱ ከትንሽ እስከ ትልቅ የምትሠራው ነገር ሁሉ፣ እግዚአብሔር ሳያውቃትና በእግዚአብሔር ዐይን ሥር ሳታልፍ አትከናወንም።

የዮሴፍ ወደ ግብፅ መሸጥ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነበርI *ዘፍጥረት 50፡ 19* እንዲህ ይላልI *"ዮሴፍም አላቸው አትፍሩI እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ ነኝን? እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝI እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።"* ዮሴፍ በግብፅ ባርያ ሆኖ የተሸጠው በእግዚአብሔር እቅድ መሠረት የእግዚአብሔርን ዓላማና እቅድ ለማከናወን ነበር። እንደገናም *"ምድርና መላዋ ለእግዚአብሔር ናትI ዓለምም በእርሷም የሚኖሩት ሁሉI" (መዝ. 23I 1)* በማለት ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝና ሀሳብ በቀር ዓለም እንደማትንቀሳቀስና የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንቅስቃሴም ከእግዚአብሔር ፈቃድ አንፃር መሆኑን ያረጋግጣል።

ዮሴፍ በተሸጠበት ጊዜ በየአንዳንዱ ሥራ የእግዚአብሔር እጅ ነበረበት። በሥላሳ ብር የገዛው ጌታው አሰኪደነቅ ድረስ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር። ሥራውም የተከናወነለት ሰው ሆነI በግብፃዊው ጌታውም ቤት ነበርና። *"ጌታውም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ እርሱ የሚሠራውንም ሁሉ እግዚአብሔር በእጁ እንዲያከናውንለት አየI" (ዘፍጥ. 39I 3)።* በባርነት በተሸጠው ሰው ላይ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን ያከናውን ነበር። የመሸሙም ነገር እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ለመሆኑ አንደኛው ትልቁ ማስረጃ ነበር። የግብፃዊው ቤት የመባረክ ዋናው ምክንያት እግዚአብሔር ዮሴፍን በላይ በመቆጣጠሩ ነበር።

ሰዎች በሁለንተናቸው እግዚአብሔርን የበላይ ሲያደርጉ ከሚሠሩት ነገር አንዱም እንኳን መሬት ላይ አትወድቅም። እግዚአብሔር ሰዎችን በበላይ ሲቆጣጠር ሥራቸውን በመባረክ ብቻ ሳይሆን በሕይወታቸው ሁሉ ድንቅ ነገር ያደርጋል። የዮሴፍ ጌታ የገዛውን ባሪያ አምኖ ከሚበላው እንጀራ በስተቀር በሁለንተናው አሰለጠነው ይላልI *(ዘፍጥ. 39I 6)።* እግዚአብሔር በዮሴፍ ሕይወት ላይ ነግሦ ስለነበር ለመሰናከያ ለሆነችው በአለቃው ሚስት እንኳን ሳይሰናከል ቀረ። በወንድሞቹ ቅናት ምክንያት የተጠላውና ከአገሩ ተሰዶ የሄደው ዮሴፍ ዘመድ ባይኖረውምI የሚወደው አባቱ ሙቷል ቢባልምI በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ስለነበር ሕያው ነበር። እግዚአብሔር ሲጠብቅ ከዘመድም ከአዝማድም በላይ ስለሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት የራሳችን ፀጉር እንኳ ያለሱ ፈቃድ እንደማትወድቅ ሁሉ በባዕድ አገር የነበረው ዮሴፍም በሄደበት ሁሉ ሥራው የተቃና ነበርI *(ማቴ. 10I 30)።*

በምቀኝነትና በሀሰት የታሠረው ዮሴፍ አሁንም የእግዚአብሔር ሞገስ ከሱ ጋር ነው። እሥረኞቹ ወደ ሚታሠሩበት ወደ ግዞት ቤት አገባውI ከዚያም በግዞት ነበርI እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበርI ምህረትንም አበዛለት። የእግዚአብሔር የበላይነት በሕይወታችን ሁሉ ካለI እሥር ቤቶችም የምህረት አደባባዮች ናቸውI ሞገስና ግርማ ከታሣሪዎቹ ፊት ስለሚፈልቅ የእሥር ቤት ጠባቂዎች ለምን እንደታሠሩ ግራ እስከሚገባቸው

ድረስ ያከብሯቸዋል። የዮሴፍንም ሁኔታ እንደዚሁ ነው የምናየው። በግዞት ቤቱ አለቃም ፊት ሞገስን ስጠውI እያንዳንዱ ዮሴፍ የሚራመድባት እርምጃ የእግዚአብሔር ክንድ እርምጃ ነበረችI *(ዘፍጥ. 39፣ 21-23)*።

ዮሴፍ እሥር ቤት እንኳን ገብቶ እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ስለነበር በመንግሥት ከተሾመው የመንግሥት ባለሥልጣን ቀጥሎ ባለሥልጣን ሆነ። የግዞት ቤቱም አለቃ በእጁ ያለውን ነገር ከቶ አላሰበም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበርና የሚያደርገውን ሁሉ እግዚአብሔር ያቃናለት ነበርI *(ዘፍጥ. 39፣ 23)*። በግብፅ ምድር በትልልቅና በትንንሽ ወንጀል ምክንያት ከታሠሩት እሥረኞች ውስጥ እንዲሁም ከአገሩ ካሉት ባለሥልጣኖች ውስጥ እንዲህ ያለውን በእጁ ያለውን ሁሉ ግርማ ሞገስ እንዲሞላ የተደረገለት ባለሥልጣን አላየንም። ከአሣሪዎቹ እስከ ታሣሪዎቹ ሁሉም ክብር የጎደላቸው፣ ግርማ ሞገስ ያጡ ነበሩ። ከታሠሩት መሐል በከፍተኛ ሥልጣን ተቀምጠው ሥራቸውን አላከብር በማለታቸው ምክንያት እሥር ቤት ውስጥ የገቡ ሰዎች ይገኛሉ። እነሱ ሁሉ ፊታቸው የጠቆረ፣ ተስፋ የቆረጡ ነበሩ። በግብፅ ምድር ያውም በእሥር ቤት በፊቱ ላይ ተስፋ የሚታይበት አንድ ሰው ብቻ ነበርI እሱም በሕይወቱ እግዚአብሔርን የበላይ ያደረገው ዮሴፍ *ነበርI(ዘፍጥ. 40፣ 6)*። ወንድሞቹ ነፍሱ እየተጨነቀች ዐይኑ እየተርገበገበች፣ አሳልፈው ለሞት ጣዕር የሰጡት ዮሴፍ አሁን በልቡ ሰላምና መረጋጋት አለ።

እሱን የሸጡት ወንድሞቹ ግን በሕይወታቸው የእግዚአብሔር የበላይነት ስላልነበር ምን አልባትም ጭንቀትና ስቃይ ነበረባቸውI *(ዘፍጥ. 42፣ 21)*። ከግብፃውያን ባላነሰ መንገድ በሕይወታቸው መረጋጋት አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዮሴፍ የሚነግረን በመከራ የነበሩት እሥረኞች እንኳን እሱን በማነጋገር መጽናናት ያገኙ እንደነበር ነው። ፍርድ በመጠባበቅ ላይ ያለው እሥረኛ በሙሉ መጽናናትን የሚያገኘው ከዮሴፍ ጋር ሲነጋገር ነበር። ዮሴፍ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር የወደፊት

የእግዚአብሔር ዕቅድ በግብፅ ምድር እንዴት እንደሚከናወን ለንጉሡ ተረጐመI *(ዘፍጥ. 41፣ 1-57)*።

ዮሴፍ በእያንዳንዱ በሚናገረው ሁሉ እግዚአብሔር ሊያደርገው ያሰበውን ያደርጋል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ሕልም ይተረጉማል ነበር የሚሰውI (ዘፍጥ. 41፣ 14-15)። ይህ ሁሉ ሆኖ አሁንም እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር። ከፍተኛ ትምህርት ተምረው በትውልድ አገራቸው የኖሩት ግብፃውያን፣ ሊሠሩትና ሊያከናውኑት ያልቻሉትን መጀመሪያም ግምጃ ቤት ጠባቂ፣ ኋላም እሥረኛ የሆነው ዮሴፍ በሚያስገርም ሁኔታ አከናወነው። ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ስለነበር ነው።

አጠቃላይ የእግዚአብሔርን የበላይነት በሕይወት ሚዛን ላይ በትክክል ለመረዳት እንዲያስችለን የሚከተሉትን ሦስትት ነጥቦች እንመለከታለን። እነዚህም፡-

1. እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ፍጹም በመሆኑ፣
2. እግዚአብሔር በአሠራሩ ፍጹም በመሆኑ፣
3. እግዚአብሔር በፍርዱና በማዳኑ ፍጹም በመሆኑ፣ ናቸው።

እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ፍጹም በመሆኑ

በዚህ በዮሴፍ ታሪክ ላይ ተመርኩዘን፣ ዮሴፍ ወደ ግብፅ የተሰደደበትን ምክንያትና በወንድሞቹ የመሸጥ መንስኤ ምን እንደሆነ ከራሱ አንደበት እንዲህ ሲል ገልጸታልI "ዮሴፍም ለወንድሞቹ እኔ ዮሴፍ ነኝI አባቴ እሰካሁን በሕይወቱ ነውን? አለ ... ዮሴፍም ወንድሞቹን ወደ እኔ ቅረቡ አለ። ወደእርሱም ቀረቡ። እንዲህም አላቸውI ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ እኔ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝI አሁንም ወደዚህ ስለሸጣችሁኝ አትዘኑI አትቆርቆሩምI

እግዚአብሔር ሕይወትን ለማትረፍ ከእናንተ በፊት ሰድዶኛልና፤" *(ዘፍጥ. 45፡ 2-6)*። የዮሴፍ ወደግብፅ በወንድሞቹ ጥበብና ማስተዋል ወይም ደግሞ ተንኮልና ምቀኝነት ሳይሆን በእግዚአብሔር እቅድ ነበር። በዮሴፍ ግንዛቤ *መሠረት*፣ እግዚአብሔር ዮሴፍ ወደ ግብፅ አገር እንዲሄድና ታላቅ ቦታ እንዲኖረው ያደረገበት ምክንያት የሸጡትን ወንድሞቹንና የነሱ የሆነውን ሁሉ ከርሃብና ከሞት ለመታደግ ነበር። ዮሴፍ እንዳለው ይህን ያደረገው በዮሴፍ ቸርነት አይደለም፤ እግዚአብሔር ዕድል ሰላዘጋጀ ያንን እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ዕድል ዮሴፍ ማከናወን ሰላለበት ነበር። በሌላ አነጋገር የእግዚአብሔርን የረጅም ጊዜ የቃል ኪዳን ዕቅድ እግዚአብሔር ሊያከናውነው የወሰነው በወንድሞቹ በተሸጠው በዮሴፍ አማካይነት ነው ማለት ነው። ይህንን ስንል በአእምሮአችን ሌላ ጥያቄ ማንሳቱ የማይቀር ነው፤ ይህም ጥያቄ ዕቅዱ ምን ነበር? አሪት ዘፍጥረት ለዚህ መልስ እለው፤ *"ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ሰደተኞች እንደሆኑ በእርግጥ ዕወቅ፤ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል። ደግሞም በባርነት በሚገዟቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ፤ ከዚያም በኋላ በብዙ ከብት ይወጣሉ፤"* *(ዘፍጥ. 15፣ 13-14)*።

ይህ የእግዚአብሔር ቃል አብርሃም ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቅርቦ ለሕዝቡ ያዘጋጀውንና የረጅሙን የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን መሆን እንዳለበት ለማወቅ ፈልጎ በጠየቀው *መሠረት* የተሰጠ መልስ ነው። በዚህ ክፍል ላይ ሌላም አስገራሚ የሆነ ነገር እናገኛለን። ይኸውም መጀመሪያ የራሳቸው እንዲሆንና እነሱ እንዲኖሩበት በእግዚአብሔር የተሰጣቸው ምድር ይሄ አሁን አብርሃም ያለበት አገር ሲሆን ተመልሰውም ሊኖሩ የሚገባቸውም በዚህ ቦታ እንደሆነ ነው።

ብዙ ሰዎች በዚህ በእግዚአብሔር ሕዝቦች አኗኗር እግዚአብሔርን እንደ እድልዎኛ በማድረግ ሌሎቹን እንዲያሳድዱ እድርጎ እነዚህን ሕዝቦች ማስቀመጡ የእግዚአብሔርነት አሠራር አይደለም የሚል እባባል አላቸው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በሥራው የማይሳሳት፣ ፍጹም እምላክ ስለሆነ በየአንዳንዱም

ተፈጥሮ የኑሮ ሚዛን ላይ የበላይ ስለሆነ፣ ይህችን ምድር ለእነዚህ ሕዝቦች ሰጥቷል። እነዚህ ሕዝቦች በፋንታው እግዚአብሔርን በትክክል ማምለክ እንዳለባቸው አስጠንቅቋቸዋል። ለዚህ ነው፣ ይህ ሕዝብ የእርሱ ባልሆነ ምድር ላይ ይሰደዳል፤ ነገር ግን እንደገና በሀብትና በበረከት ይመለሳል ያለው።

ስለዚህ ጥያቄያችን አሁን መልስ አገኘ፤ የእግዚአብሔር ዕቅድ የእነዚህን ሰዎች ስደት ባሉበት መቆጣጠርና ከዚያም እንዲመለሱ ቸርነትንና ምህረትን ማድረግ ነው የፈለገው። ለዚህም ሥራ የተመደበው ሰስደቱ አቀባበል ዮሴፍ ሲሆን ለመውጣቱ ደግሞ ሌላ ሰው ያዘጋጃል። አሁንም ከዚያው ከዘፍጥረት ሳንወጣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዴት ወደ ግብፅ አገር እንደሄደ የሚለንን እንመልከት። *"እግዚአብሔርም በሌሊት ራዕይ ያዕቆብ ሆይ ብሎ ለእሥራኤል ተናገረው እርሱም እነሆኝ አለ። አለውም የአባቶችህ አምላክ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ወደ ግብፅ መውረድ አትፍራ፤ በዚያ ትልቅ ሕዝብ አደርግሃለሁና፤ እኔም ወደ ግብፅ አብራህ እወርዳለሁ፤ ከዚያም ደግሞ እኔ እወጣሃለሁ፤"* *(ዘፍጥ. 46፣ 2-4)*።

እግዚአብሔር አይሳሳትም፤ የሚሠራቸው ሁሉ በዕቅድ ነው። ያዕቆብ ምንም እንኳን አገሩ ርሃብ ቢሆን ወደ ግብፅ መውረድን ስላልፈለገ እዚያው በፍልስጤም ሆኖ ሞትን መርጦ ነበር። እግዚአብሔር ግን ዮሴፍን እንደተናገረው፣ መጀመርያ ያዕቆብ የሚወደው ልጁ በወንድሞቹ እንዲሸጥ ያደረገው ለዚሁ ዓላማ ብሎ እንደሆነ አሁንም እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሚነግረው ያንኑ እውነት እንደሆነ እንረዳለን።

እግዚአብሔር ግብፅ የሚያስፈራ አገር አይደለም፤ እንደኛ እኔ ከእንተ ጋር ነኝ፤ እብሬ ከዚያ እወርዳለሁ። ሁለተኛ አንተ የምትወደው፣ ወንድሞቹ ግን የጠሉትና የሸጡት፣ ለብዙ ዘመን ያዘንክበት ልጅህ ዮሴፍ በዚያ ስለሆነ እሱ እንዲቀበልህ ተዘጋጅቷል። ከዚያም ስትሄድ ትልቅ ሕዝብ እደርግሃለሁ ነው የሚለው። በዚህም በእግዚአብሔር ቃል *መሠረት* ሁለት መሠረታዊ ነገሮች ለያዕቆብ ተሰናድተውለት ነበር። ዋናውና የመጀመርያው

የሚወደው ልጁ ዮሴፍ የግብፅ አገር ገዥ ነው። ሁለተኛም፣ በግብፅ አገር የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት የሰው ኃይልን ጨምሮ የሚተዳደረውና የሚታዘዘው በዮሴፍ ነው።

ዮሴፍ በፈርያን ዘንድ ታማኝ ከመሆኑ የተነሣ እንኳን የሱ ዘመዶች መጡ ተብሎ የሱ ነገር አለበት የተባለው ሁሉ ይከበር ነበር። በዚህም ምክንያት ሁለተኛውና ጠቃሚው ነገር ለያዕቆብ ለምና ምቹ የሆነውን ቦታ የማግኘት ዕድል እንዲያገኝ ሆነ። እግዚአብሔር እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ሲል እነዚህን ሁሉ መንገዶች አመቻችቶ እንጂ እንዲሁ ዝም ብሎ አልነበረም።

ዮሴፍና ያዕቆብ በነበሩበት ጊዜ እሥራኤላውያን በግብፅ አገር ትልቅ ቦታና ሀብት እንደነበራቸው መረዳት አንችላለን። ዮሴፍ ይህንን ነገር አረጋግጧልI ዮሴፍ አባቱ ሆይ እኔ በግብፅ አገር ገዥ ስለሆንኩኝ የምትፈልገውን ቦታና ሀብት እሰጥሃለሁI በዚህ በግብፅ በሕይወት እስካለህ ደስ ብሎህ እንድትኖር አደርግሃለሁ በማለት ገልጾአል *(ዘፍጥ. 45፣ 28-34)*።

ፈርያንም እሥራኤላውያን ወደ ግብፅ አገር ሲገቡ ትልቅ ቦታና ክብር እንደሰጣቸው ይኸው ኦሪት ዘፍጥረት ያስረዳል። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ምን አልባትም ለሦስት መቶ ዓመት ያህል ያለ ምንም ችግር እንደኖሩ መገመት እንችላለን። ከዚያ በኋላ ግን ምን ዓይነት ለውጥ እንደመጣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን አለው። *"ዮሴፍም ሞተI ወንድሞቹም ያም ትውልድ ሁሉ። የእሥራኤልም ልጆች አፈሩI እጅግም በዙ ተባዙምI እጅግም ፀኑ ምድሪቱም በነሱ ሞላችI" (ዘፀአ. 1፣ 6-7)*።

በዚህ ቃል መሠረት ዮሴፍና ወንድሞቹም ከሞቱ በኋላ እሥራኤላውያን በዙ፣ እጅግም ፀኑ። ይህም መራባትን፣ መባዛትን፣ በምድር መሙላትን የሚያሳይ ሲሆን፣ ፀኑ የሚለው ደግሞ ብርታትን፣ ኃይልን፣ ኢኮኖሚን፣ በጠቅላላ ለጠላት አይበገሬነትን ለወዳጅ ደግሞ መመኪያነትን የሚያሳይ ነገር ነው። በአንድ አረፍተ ነገር ሲጠቃለል እግዚአብሔር ለአብርሃም ልክ

እንደተናገረው እሥራኤላውያንን በሁለንተናዉ መልኩ ምሉዕ አድርጓቸዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ፣ የተናገረውን የሚፈጽም አምላክ ነው። እጅግ ይበረታሉ ብሏል፣ በርትተዋልI ይበዛሉ ብሏል፣ በዝተዋልI ያፈራሉ ብሏል፣ ንብረት አላቸው። አሁን የሚቀረው ወዴት ነው የሚሄዱት ነው።

ከዚህ ሁሉ በኋላ እግዚአብሔር ታሪክን ሲቀይር እናያለን። በሰው ሃሳብና አእምሮ የማይቻል አስቸጋሪና የጨለማ ጊዜ ሲሆን ከዚያ አልፎ ግን እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ጠባቂና በቃል ኪዳኑ የሚቆም አምላክ መሆኑን ሲፈጽም እንመለከታለን። ታሪኩን ኦሪት ዘፀአት እንዲህ ብሎ ነው የሚጀምረው። በግብፅም የዮሴፍን ያላወቀ አዲስ ንጉሥ ተነሣ። ንጉሡ አሥራኤልን የሚፈራ እሥራኤል ከመብዛታቸው የተነሣ ምድሪቱን ያስጨንቋትና ያስጠቧት በመሆኑ ለአገሪቱና ለመንግሥቱ አስጊ መሆናቸውን የሚያውጅ፣ ለዚህም ይጠቅማል የተባለ በሰው አእምሮ የተዘጋጀ ጥበብ የተጠበበ ሰው ነበር። ቀጥታ ቃሉን ከኦሪት ዘፀአት እንየውI *"እርሱም ሕዝቡን እነሆ የእሥራኤል ልጆች ሕዝብ ከእኛ ይልቅ በዝተዋልI በርትተውማልI እንዳይበዙI ሰልፍም በተነሣብን ጊዜ ጠላቶቻችንን አግዘው እንዳይወጉንI ከምድሪቱም እንዳይወጡI ኑ እንጠበብባቸው አሰI" (ዘፀአ. 1፡ 10)*።

ይህን ታሪክ ስናነብ መደነቃችን የማይቀር ነው። አሁን በአሜሪካን አገር የሚኖሩ ከሌላ አገር የመጡ ሀብታሞች ያፈሩትን ሀብትና ንብረት እንዲበዛላቸው በማገበርና በልዩ ልዩ ባሕል እንዲጠናከሩ ካደረጉና ከተጠናከሩ በኋላ ያንን አሠራራቸውን የሚቃወም መንግሥት ሊመጣ ይችል ይሆን? ይህንንስ ይመጣል ብለው ያስቡ ይሆን? ወይም በሌላ አነጋገር አሁን በገንዘብና በዕውቀቱ እንደልቡ ሠርቶ ሀብታም መሆን የማያስቸግረው የአሜሪካን ሕግ ተቀይሮ አዋቂዎቹንና ሀታሞቹን የሚቆጣጠርና የሚያሰጨንቅ ሕግ ቢሆን ምን ይሆናል? በእሥራኤል የተደረገው ይህ ነው።

እሥራኤላውያን ሰግብፅ አገር በነበሩ ጊዜ ሦስትና አራት ትውልድ ካለፈ፣ አገሩም አገራችን ነው ብለው ከተዝናኑ ከየት እንደመጡ አንኳን ማወቅ የማይችሉ ትውልዶች ከሆኑና ለአገሪቱ ባለውለታነታቸውን አረጋግጠናል ካሉ በኋላ እንዲህ ዓይነት አስጨናቂ አዋጅ ይወጣል ብሎ ማን ይገምታል። በንጉሡ ሃሳብ መሠረት ለአዋጁ መነሻ የሆነው አንደኛ እሥራኤላውያን በርትተዋል፣ ሁለተኛ በዝተዋል፣ እነዚህ ከውሰጥ ሲሆኑ መንግሥቱ ደግሞ በውጭ ጠላቶች የተወጠረ ይመስላል። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነን ጆሲፋስ የተባለው የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ ኢትዮጵያውያን በዚያን ዘመን ግብፅን እሰከ ዋና ከተማዋ ወረዋት እንደነበረ መመዝገቡ ነው።

ጠላት በተነሣብን ጊዜ እሥራኤላውያን እንዳይተባበሩና እንዳይደመሰሱን ነው የሚለው። ስለዚህ እሥራኤላውያን እንዳይበዙ ብቻ ሳይሆን ከአገሪቱ እንዳይወጡ መጠበብ አለብን ነው የሚለው። ይህ ንጉሥ መብዛታቸውንስ ቁጥራቸውን አይቶ ይወቅ፣ መበርታታቸውንም ድርጅታቸውን አይቶ ይረዳ፣ መውጣታቸውን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ቃል ኪዳን የሱ ባልሆነ አገር ይኖራሉ፣ ከዚያም ይበዛሉ፣ እንደገናም ይጨቆናሉ፣ በመጨቆናቸውም ምክንያት እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው በኃይሉና በችሎታው ነፃ ያወጣቸዋል። ስለዚህ ይህ የቃል ኪዳን መከናወኛ ጊዜ ደረሰ ማለት ነው። ፈርያን ይህንን የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን መድረሱን የሚያሳውቅ አዋጅ ነጋሪ ነበር፣ ስለዚህም ነው ፈርያን እንዲህ ያሰው፣ *"ኑ አንጠበብባቸው፣ .... ከዚያም በብርቱ ሥራ ያስጨንቋቸው ዘንድ ግብር አሰገባሪዎቹን ሾመባቸው፣"* ይላል። *(ዘፀአ. 1፣ 10-13)*።

እግዚአብሔርም ተናግሯል፣ በኃይል በባርነት ያሰጨንቋችኋል ብሏል፣ ነገር ግን በጭንቀት ውሰጥም እግዚአብሔር ሰላለ፣ በመከራ ውሰጥም እግዚአብሔር ሰለሚሠራ ቃሉ፣ እንደሚለን እንዳሰጨነቋቸው መጠን እንዲሁ ብዙ ሰው

ተሰፋ ቢቆርጥም፣ ነገሮች ሁሉ ያለቀላቸው ቢመስሉም፣ እግዚአብሔር ሥራውን አያቆምም። ቃል ኪዳኑንንም አያጥፍም፣ ይሰዛሉ ብሏል እየበዙ ነው፣ ይጨነቃሉ ብሏል፣ እየተጨነቁ ነው፣ መብዛታቸውንም ጭንቀታቸውንም እግዚአብሔር የበላይ ሆኖ ይቆጣጠራል።

ጊዜው አስፈሪ ነበር፣ ታሪኩን ሰናጠናው ለእሥራኤላውያን መልካም ጊዜ አልነበረም። አንዱ አዋጅ በሥራ ላይ ሳይውል ሌላው እየተተካ በየቀኑ የሚወጣው የአዋጅ ቃል የእሥራኤላውያንን አእምሮ የሚያጨልም ለጀሮና ለጎሲናም የሚከብድ ነበር። መብዛታቸው ቢቀጥልም፣ መከራቸው ያን ያህል ጨምሯል፣ የጉልበት ሥራው በእጥፍ እንዲጨምር ተደርጓል። ይህንን ከማሙ ለማድረሰ አዳዲሰ የከተማ ፕሮጀክቶች ተተክለዋል፣ በነዚያ ከተማዎች እሥራኤላውያን በከባድ ሥራ ነፍሳቸውን እንዲያጡ ተደርገዋል፣ *(ዘፀአ. 1፣ 14)*።

አሁንም እሥራኤላውያን እየበዙ ነው። ቀጣዩ አዋጅ ወንድ ሕፃን ልጅ ሲወለድ ገና ብርሃንን አንዳየ ታንቆ እንዲገደል በአዋላጆች ሰም ነፍሰ ገዳዮች ተመደቡ፣ ነገር ግን እንዲገድሉ የተመደቡት አዋላጆች እግዚአብሔርን ፈሩ። የንጉሣን ትእዛዝ አላደረጉም ይላል። በመከራውም ውሰጥ የእግዚአብሔር እጅ አለች፣ መልካም ላደረጉትም እግዚአብሔር መልካም አደረገላቸው። ቸር አምላክ ሰለሆነ ሰሱ ተማምነው መልካም ለሚያደርጉ፣ በሱም ተማምነው በመከራ ውሰጥ ላሉት ለሁሉም መንገድ አለው። በሰው አእምሮ ግን ይህ ነገር ያልፋል ብሎ መገመት አዳጋች ነው። ማን ሊያምን ይችላል? ከአራት ትውልድ በኋላ ወደተረሣ አገር የመግባት ሁኔታ ይመጣል ብሎ።

መታየት ያለበት፣ የኮሎምቦሰ ልጆች ዛሬ ከአሜሪካ ወጥተው ወደ መጡበት አገር ተመልሰው ሕዝብ እንዲሆኑ እንደ ማሰብ ነው። በሰው አእምሮ ሲታሰብ ከባድ ነው፣ ሊደረግም፣ ሊሆንም አይችልም። እንኳን ይህን ያህል ጊዜ የቆዩት ይቅርና እኛ እንኳን የመጀመሪያ ትውልዶች እንዲያውም ንብረትና ቤት ያለን፣

ፓስፖርታችንን ያላስቀየርነው፣ የቪዛ ቀናችን እንኳን ያላለፈው፣ በእንደዚህ ዓይነት አስገዳጅነት ሁኔታ ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ ብንባል ይከብዳልI በእግዚአብሔር አሠራር ግን ሁሉም ነገር ቀላል ነው።

እግዚአብሔር ይህን ሁሉ ያደረገው ቃል ኪዳኑን የሚያስብና የሚጠብቅ አምላክ ስለሆነ ነው። *በዘፍጥረት 26፣ 3-4* የሚከተለውን እናነባለንI *"እኔ ካንተ ጋር እሆናለሁ፣ እባርካለሁም፣ እነዚህንም መንደሮች ሁሉ ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁና ለአባትህ ለአብርሃም የማልኩለትን መሃላ አፀናለሁ።"*

እግዚአብሔር ከማለ ከተናገረ በሃሳቡ የፀናና ሃሳቡን የሚያደርግ አምላክ ነው። እኔ ከአንተ ጋር ነኝ ያለውን አብርሃምን ከዘሩም ጋር አብሮ እንደሚኖር ቃል ስለገባ በየትኛውም አገርና ጊዜ ቢሆኑ፣ ምንም ዓይነት አሰቸጋሪ ነገር ቢያጋጥም እግዚአብሔር ከነሱ ጋር ነው። ዘፍጥረት 28፣ 15 ይህንኑ ሃሳብ ያፀናል። *"እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ በምትሄድባት መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁI ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁI የነገርኩህን እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።"* እግዚአብሔር ከስደተኞች ግር አብሮ በስደት አለI ከታሠሩት ጋር አብሮ በእሥር ቤት አለI ከታመሙትም ጋር አብሮ በአልጋ ላይ ይኖራል። እግዚአብሔር የማለው ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር ነኝ በሚል ነው። *ዘፍጥረት 31፣ 3 "እግዚአብሔርም ያዕቆብን ወደ አባትህ ምድር ወደ ዘመዶችህም ተመለስ፣ ከአንተም ጋር እሆናለሁ አለው"* ይላል። እግዚአብሔር በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ሊያደርገው የገባውን ቃል ሳያከናውን አይተወውም። ይህ ሁሉ ነገር ሰውን የመውደዱና ከሰው ጋር ቃል ኪዳን የመግባቱ ፈቃድ፣ ቢያደርጉልኝ ላድርግላችሁ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነፃ ፈቃድ ከራሱ ነፃ ሥጦታ የመነጨ (የፈለቀ) ነው።

ይህንን ቃል ኪዳን ሲገባ ሊያደርገው የሚችል መሆኑን ማረጋገጫ ምልክቶች ነበሩ። ከኖኅ ጋር ቃል ኪዳን ሲገባ እግዚአብሔር ወደፊት ዓለምን በፍል ውሃ እንደማያጠፋ ከራሱ

በመነጨ ፈቃድ የቀሰተ ዳመና ምልክት አድርጎ ነበርI *(ዘፍጥ. 9፣ 12-14)።* አብርሃም ባቀረበው መስዋዕት በማህሉ በማለፍ ሊያደርግ ያሰበውንና ያቀደውን እንደሚያደርግ ወስኗልI *(ዘፍጥ. 15፣ 13-15)።* በሐዲስ ኪዳን ፍጡራን በሆኑና በሚያልፉ ምልክቶች ሳይሆን፣ ዘለዓለማዊ በሆነው በማያረጀውና ሁልጊዜ በሚኖረው በራሱ ማንነት ነው የሚምለው።

የእብራውያን ጸሐፊ እንዲህ ይገልፀዋል። እግዚአብሔርም ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ በእውነት እየባረኩኝ እባርክሃለሁI እያበዛሁም አበዛሃለሁI ብሎ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ በራሱ ማለ። ስለዚህ እግዚአብሔር በቃል ኪዳን ለዘለዓለም ከሕዝቡ ጋር እንደሆነና እንደሚሆን በገባው ቃል መሠረት ለዘለዓለም ከእኛ ጋር ነውI *(ማቴ. 1፣23)።* *"አማኑኤል"* በማለት እግዚአብሔር ለዘለዓለም ከእኛ ጋር መሆኑን የሚያረጋግጥ የቃል ኪዳን ዋስትና ነው። ይኸው ወንጌል በመደምደሚያው ላይ እስከ ዓለም ፍጻሜ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝI በማለት እግዚአብሔር በቃል ኪዳን ሁል ጊዜም ከሰዎች ጋር እንደሆነና ያም ደግሞ እንደማይለወጥ፣ ፍጹምም እንደሆነ የምንረዳበት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በሕይወት ሚዛን ላይ የበላይ ነውI የምንለው በቃል ኪዳኑ ፍጹም ስለሆነ ነው።

<u>በአሠራሩ ፍጹም በመሆኑ</u>

በትንቢተ ኢሳይያስ የተነገረው *"ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር እሱም ምድርን የሠራ ያደረገ፣ ያፀናትም መኖርያ ልትሆን እንጂ ለከንቱ እንዳትሆን ያልፈጠራት አምላክ እንዲህ ይላልI እኔ እግዚአብሔር ከእኔ በቀር ሌላ የለም ይላልI"* በማለት አስፍሯልI *(ኢሳ. 45፣ 18)።*

እግዚአብሔር ፍጹምና እዋቂ በሥራውም እንከን የሌለበት በመሆኑ የፈጠረው ፍጥረት በሙሉ ሥራና ዓላማ አለውI እንዱ በእንዱ ላይ ሌላውም ለእንዱ ጠቀሜታና ጌጥ እንዲሆን ተደርጎ ነው የተሠራውII *"የያዕቆብ ዕድል ፋንታ እንደዚህ አይደለምII እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና፣ እሥራኤል የርስቱ ነገድ ነውና ሰሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነውI" (ኤር. 10፣16)II* እግዚአብሔር የሚለው ስም ራሱ ያለና የሚኖር እኔ ነኝ ብሎ ለሙሴ የሰጠው ከርሱ በቀር ሌላ የሌለ፣ እሱ ብቻውን ለሁሉ በሁሉም በቂ እንደሆነ የሚያስረዳ ትምህርት ነውII

እኔ የሚለው ቃል ራሱ በዮሐንስ ወንጌል እኔ የዓለም ብርሃን ነኝI እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝI እኔ በር ነኝI እኔ መንገድ ነኝI እኔ የወይን ግንድ ነኝI በሚል እርሱ ሕይወትም ብርሃንም መንገድም እንደሆነ የሚገልፅ ነውI *(ዮሐ. 8፣ 12)II* ይህንን ካየንና ከተረዳን እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ በብሉይ ኪዳን እንዴት እንደሠራና እንዴት እንደጠበቃቸው መመልከት እንችላለንII እግዚአብሔር ራሱ ፍጹምና ሥራውም እንከን የለሽ ስለሆነ እርሱ በፈለገው መንገድ የፈለገውን ሰው እርሱ ለሚፈልገው ሥራ ይጠቀምበታልI የሙሴ ታሪክ የሚያስረዳን ይህንን ነውII እስፈሪ ከሆነው ከፈርዖንና እስጨናቂ ከሆነችው ከግብፅ እሥራኤልን ነፃ ማውጣት የሙሴ ችሎታ አልነበረምII ነገር ግን እግዚአብሔር ፍጹምና በሥራው የማይሰሳት ስለሆነ ላለመታዘዝ ብዙ ምክንያት ያቀረበውን ሙሴን ትንሽና ዝቅተኛ በሆነው በግ በሚጠብቅበት በትር ተአምራት በማድረግ የእሥራኤልን ነፃነት እንዳቀዳጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናልI *(ዘፀ. 4፣ 1-5I 12፣ 35-36)II*

እግዚአብሔር በእሥራኤሉ ፍጹም ስለሆነ ለአራት መቶ ዓመት ባሪያ አድርገው የገዟቸው አለቆቻቸው በፈቃደኝነት ያልሰጧቸውን ደመወዛቸውን ነፃ በሚለቋቸው ጊዜ ወንዱ ከጌታውI ሴቷ ከእመቤቷ የሚችሉትን ያህል እንዲቀበሉ እግዚአብሔር ወሰነII መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ቃል ይነግረናልI *"የእሥራኤል ልጆች ሙሴ እንዳዘዘ አደረጉI ከግብፃውያንም የብርንና የወርቅን ዕቃ ልብሰንም ለመኑII እግዚአብሔርም ለሕዝቡ*

በግብፃውያን ፊት የፈለጉትን እንዲሰጡአቸው ሞገሰን ሰጠII እነሱም ግብፃውያንን በዘበዙI" (ዘፀአ. 12፣ 35-36)II

በፈቃደኝነት ሥራ በሠሩበት ጊዜ ያልሰጧቸው ግብፃውያን አሁን እግዚአብሔር በእሠራሩ ፍጹም ስለሆነ ዳኛም ጠበቃም ሆኖ የደከሙበትን እንዲወሰዱ አደረገII ምንም እንኳን ግብፃውያን ለጊዜው ቢለቋቸውም በመጸጸትና በመቆርቆር ተከታትለው ሊያጠፏቸው ፈልገው ነበርII እግዚአብሔር ግን በእሠራሩ ፍጹም ስለሆነ ደካማው በጉልበታሙ እንዳይበደል ዳኛም ስለሆነ ለእሥራኤላውያን በመዋጋት እሥራኤላውያንን በባሕር እሻገራቸውII ሙሴ የእሥራኤልን ጩኸት ሲያቀርብ፣ እግዚአብሔርም ሙሴን አለውI ለምን ትጮህብኛለህ? እንዲንዙ ለእሥራኤል ልጆች ንገርI አንተም በትርህን እንባ፣ እጅህንም በባሕሩ ላይ ዘርጋI ከፈለውም የእሥራኤል ልጆች በየብስ ያልፋሉI *(ዘፀአ. 14፣ 15-16)II*

ባሕርን ደረቅ የሚያደርግ፣ በተናቀና እዚህ ግባ በማይባል መሣሪያ ተአምራት የሚሠራ፣ ሥራው ፍጹም ከሆነው ከእግዚአብሔር በቀር ማን ያደርጋል? የሳሙኤል እናት ሀና ስለእግዚአብሔር አዋቂነትና ፍጹምነት እንዲህ ትላለችI *"...እግዚአብሔር እዋቂ ነውና እግዚአብሔር ሥራውን የሚመዝን ነውና ከአፋችሁ የኩራት ነገር አይውጣI" (1ኛ ሳሙ. 2፡ 3)II* ይህች በሰዎች ዘንድ ተዋርዳ የነበረች ልቧ በሐዘን ተሰብሮ የደስታ ጊዜ እጥታ ተጨንቃ የነበረች ሴት እግዚአብሔር ሲጎበኛትና እውነተኛ ሥራውንም ስታይ ለእምላኳ ያቀረበችው መዝሙር ነበርII

የሀና ሕይወት በጣም አሳዛኝ ሕይወት እንደሆነ በምዕራፍ 1 ቁጥር 6 ላይ እናነባለንII እንደገና በዚህ ምዕራፍ ቁጥር 11 ላይ *"...እቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ፣ የባሪያህን መዋረድ ተመልከተህ ብታስበኝ፣ እኔንም ባትረሳ፣ ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ፣ እድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ...I" (1ኛ ሳሙ. 1፣ 11)II* ይህንን ፀሎት ፀልያ አምላኳ ጎብኝቷት ያቀረበችው

እግዚአብሔር ፍጹምና እዋቂ በሥራውም እንከን የሌለበት በመሆኑ የፈጠረው ፍጥረት በሙሉ ሥራና ዓላማ አለውI እንዱ በእንዱ ላይ ሌላውም ለእንዱ ጠቀሜታና ጌጥ እንዲሆን ተደርጎ ነው የተሠራውII *"የያዕቆብ ዕድል ፋንታ እንደዚህ አይደለምII እርሱ የሁሉ ፈጣሪ ነውና፣ እሥራኤል የርስቱ ነገድ ነውና ሰሙ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነውI" (ኤር. 10፣16)II* እግዚአብሔር የሚለው ስም ራሱ ያለና የሚኖር እኔ ነኝ ብሎ ለሙሴ የሰጠው ከርሱ በቀር ሌላ የሌለ፣ እሱ ብቻውን ለሁሉ በሁሉም በቂ እንደሆነ የሚያስረዳ ትምህርት ነውII

እኔ የሚለው ቃል ራሱ በዮሐንስ ወንጌል እኔ የዓለም ብርሃን ነኝI እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝI እኔ በር ነኝI እኔ መንገድ ነኝI እኔ የወይን ግንድ ነኝI በሚል እርሱ ሕይወትም ብርሃንም መንገድም እንደሆነ የሚገልፅ ነውI *(ዮሐ. 8፣ 12)II* ይህንን ካየንና ከተረዳን እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ በብሉይ ኪዳን እንዴት እንደሠራና እንዴት እንደጠበቃቸው መመልከት እንችላለንII እግዚአብሔር ራሱ ፍጹምና ሥራውም እንከን የለሽ ስለሆነ እርሱ በፈለገው መንገድ የፈለገውን ሰው እርሱ ለሚፈልገው ሥራ ይጠቀምበታልI የሙሴ ታሪክ የሚያስረዳን ይህንን ነውII እስፈሪ ከሆነው ከፈርዖንና እስጨናቂ ከሆነችው ከግብፅ እሥራኤልን ነፃ ማውጣት የሙሴ ችሎታ አልነበረምII ነገር ግን እግዚአብሔር ፍጹምና በሥራው የማይሰሳት ስለሆነ ላለመታዘዝ ብዙ ምክንያት ያቀረበውን ሙሴን ትንሽና ዝቅተኛ በሆነው በግ በሚጠብቅበት በትር ተአምራት በማድረግ የእሥራኤልን ነፃነት እንዳቀዳጃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናልI *(ዘፀ. 4፣ 1-5I 12፣ 35-36)II*

እግዚአብሔር በእሥራኤሉ ፍጹም ስለሆነ ለአራት መቶ ዓመት ባሪያ አድርገው የገዟቸው አለቆቻቸው በፈቃደኝነት ያልሰጧቸውን ደመወዛቸውን ነፃ በሚለቋቸው ጊዜ ወንዱ ከጌታውI ሴቷ ከእመቤቷ የሚችሉትን ያህል እንዲቀበሉ እግዚአብሔር ወሰነII መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ የሚከተለውን ቃል ይነግረናልI *"የእሥራኤል ልጆች ሙሴ እንዳዘዘ አደረጉI ከግብፃውያንም የብርንና የወርቅን ዕቃ ልብሰንም ለመኑII እግዚአብሔርም ለሕዝቡ*

በግብፃውያን ፊት የፈለጉትን እንዲሰጡአቸው ሞገሰን ሰጠII እነሱም ግብፃውያንን በዘበዙI" (ዘፀአ. 12፣ 35-36)II

በፈቃደኝነት ሥራ በሠሩበት ጊዜ ያልሰጧቸው ግብፃውያን አሁን እግዚአብሔር በእሠራሩ ፍጹም ስለሆነ ዳኛም ጠበቃም ሆኖ የደከሙበትን እንዲወሰዱ አደረገII ምንም እንኳን ግብፃውያን ለጊዜው ቢለቋቸውም በመጸጸትና በመቆርቆር ተከታትለው ሊያጠፏቸው ፈልገው ነበርII እግዚአብሔር ግን በእሠራሩ ፍጹም ስለሆነ ደካማው በጉልበታሙ እንዳይበደል ዳኛም ስለሆነ ለእሥራኤላውያን በመዋጋት እሥራኤላውያንን በባሕር እሻገራቸውII ሙሴ የእሥራኤልን ጩኸት ሲያቀርብ፣ እግዚአብሔርም ሙሴን አለውI ለምን ትጮህብኛለህ? እንዲንዙ ለእሥራኤል ልጆች ንገርI አንተም በትርህን እንባ፣ እጅህንም በባሕሩ ላይ ዘርጋI ከፈለውም የእሥራኤል ልጆች በየብስ ያልፋሉI *(ዘፀአ. 14፣ 15-16)II*

ባሕርን ደረቅ የሚያደርግ፣ በተናቀና እዚህ ግባ በማይባል መሣሪያ ተአምራት የሚሠራ፣ ሥራው ፍጹም ከሆነው ከእግዚአብሔር በቀር ማን ያደርጋል? የሳሙኤል እናት ሀና ስለእግዚአብሔር አዋቂነትና ፍጹምነት እንዲህ ትላለችI *"...እግዚአብሔር እዋቂ ነውና እግዚአብሔር ሥራውን የሚመዝን ነውና ከአፋችሁ የኩራት ነገር አይውጣI" (1ኛ ሳሙ. 2፡ 3)II* ይህች በሰዎች ዘንድ ተዋርዳ የነበረች ልቧ በሐዘን ተሰብሮ የደስታ ጊዜ እጥታ ተጨንቃ የነበረች ሴት እግዚአብሔር ሲጎበኛትና እውነተኛ ሥራውንም ስታይ ለእምላኳ ያቀረበችው መዝሙር ነበርII

የሀና ሕይወት በጣም አሳዛኝ ሕይወት እንደሆነ በምዕራፍ 1 ቁጥር 6 ላይ እናነባለንII እንደገና በዚህ ምዕራፍ ቁጥር 11 ላይ *"...እቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ፣ የባሪያህን መዋረድ ተመልከተህ ብታስበኝ፣ እኔንም ባትረሳ፣ ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ፣ እድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ...I" (1ኛ ሳሙ. 1፣ 11)II* ይህንን ፀሎት ፀልያ አምላኳ ጎብኝቷት ያቀረበችው

መዝሙር ነበር ከላይ የጠቀስነው። በዚሁ በመዝሙሯ ላይ ስለ እግዚአብሔር የምትለው ነገር አላት፤ "እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና፣ እንደ አምላካችን ጻድቅ የለምና፣ ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም፤" (1ኛ ሳሙ. 2፣ 2)። የእግዚአብሔር ስዎች የእግዚአብሔርን ቅድስናና ፍጹም ሥራውን ሲመለከቱ የሚያቀርቡት መዝሙር ነው፤ የእመቤታችን ጸሎትም ይህንኑ የሚያስረዳ ነው።

ከመልአኩ የምስራች ሰላምታ ስትሰማ እግዚአብሔር እንደጐበኛት በኤልሳቤጥ ሲነገራት ነፍሴ ጌታዬን ታከብረዋለች አለች፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታልቅ ሥራን አድርጓልና። የእግዚአብሔር አሠራር ከሰው አእምሮ በላይ ነው፤ ነገር ግን ፍጹምና የማይሰሳት ነው። በዘመናችንም ስንመለከት የሰው ልጅ ምንም ያህል ቢራቀቅ የቱንም ያህል ጥበብ ቢጨምር ከእግዚአብሔር አሠራር አይደርስም። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ በላከው መልዕክት "እንግዲህ እንደ ወንጌሌ ሰለ ኢየሱስ ክርስቶስም እንደ ተሰበከ፣ ከዘለዓለም ዘመንም የተሰወረው አሁን ግን የታየው በነቢያትም መጻሕፍት የዘለዓለም እግዚአብሔር እንዳዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀው ምስጢር እንደተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለው፣ ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አሰከ ዘለዓለም ድረስ ክብር ይሁን፣ አሜን፤" (ሮሜ 16፣ 25-27)።

ጳውሎስ የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ፤ ተብሎ ተጽፏልና ጥበበኛ የት አለ? ጸሐፊስ የት አለ? የዚህች ዓለም መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚህችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንደሆነ አላደረገምን? (1ኛ ቆሮ. 1፣ 18-21)። የደህንነትን ትምህርት ስናይ በሰው አስተሳሰብ እጅግ የተናቀና እዚህ ግባ የማይባል አሠራር ነው። ይህ በሰው ዐይን የተናቀና ዝቅተኛ ነው የተባለው ነገር ነበር ራሱን ከፍ ከፍ ለሚያደርገው የሰው ልጅ ሞኝነት መስለ። ነገር ግን እሱ ከጥበብ ሁሉ በላይ ጥበበኛ ነበር። ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ እንዲህ ሲል ገልጾታል፤ "ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር

የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ፤ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምንም ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ፤" (1ኛ ቆሮ. 1፣ 27-29)።

ከክርስትና ትምህርት የምናገኘው ትልቁ ነገር በዓለም ላይ ምንም ቢደረግ፣ ምንም ቢሠራ፣ ቢደከም በሰው የተሠራ ሁሉ የሚያረጅ፣ የሚያልፍና የሚጠፋ አንድ አንድ ጊዜም ከተሠራ በኋላ ፀፀት የሚያመጣ ፍጹምነት የሌለው ነው። ነገር ግን የተሠራው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድና ሃሳብ ከተሠራ ፍጹምነት አለው። በየዘመኑ/በየትውልዱ አዋቂዎችና እንከን የሌላቸው ስዎች ተነስተዋል፤ ብዙ ሥራም ሠርተዋል። ነገር ግን እነርሱ ቢያልፉ ተከታዩ ትውልድ የነሱን ሥራ ካላስተካከለውና ካላረመው በቀር አንዳንዴም ጠቅላላ ካልለወጠው በቀር እንዳለ ቀጣዩን ትውልድ ሊጠቅም አይችልም።

የእግዚአብሔር አሠራር ግን አንድ ጊዜ ይሁን ብሎ ያደረገው ነገር እርሱ ዘለዓለማዊ ነው፤ አነስ ተብሎ አይጨመርበትም፤ በዛ ተብሎም ሊቀነስ አይችልም። ስለዚህ የሰው ልጅ በዚህ ዓለም እየኖረበት ያለውን ዕድሜውን በእግዚአብሔር አሠራር ላይ ካልመሠረተው ሕይወት ሊዛባ ይችላል። ጉልበትም ቢሆን ይደክማል፤ ገንዘብም ቢሆን ያልቃል፤ ወገንም ቢሆን ይጣላል፤ የራስ ሃሳብም ቢሆን ይለዋወጣል፤ የእግዚአብሔር ሃሳብ ግን ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል።

ለዓለም ዛሬ የተሠወረው ትልቁ ምስጢር ይህ ነው። ዓለም የደከመውን ያህል ደግሞ የተማረውን ያህል ተምሮ የሚችለውን ያህል ወጭ አውጥቶ ያገኘው ነገር እግዚአብሔር ከሠራው በጣም ጥቂቱን ነው። ዛሬ ባለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም በሁለንተናው ተለውጧል። የሰው ልጅ ራሱን ለማስደሰት ብዙ ነገሮች ሠርቷል፤ ከመኖሪያ ቤት እስከ መገናኛ፣ ትልልቅ ትምህርት ቤቶችን በጠቅላላ ይጠቅመኛል የሚለውን ገንብቷል።

ድሮ ከሦስት እስከ አራት ወራት የሚጨርሱት የመገናኛ ዘዴዎች 8 እና 10 ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የመገናኘትና የሃሳብ ልውውጥ የማድረጉን ዕድገት ስንመለከት ምን ያህል ትልቅና ክፍተኛ እንደሆነ እንረዳለን።

ሰው ራሱን ለማስደሰት የተለያዩ ነገሮችን በመፍጠር ላይ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ይጠቅማል ብሎ አንድ ጊዜ የሠራውን በማበላሸት ላይ ነው። ባለፈው የአሜሪካን የሰማይ ጠቢባን የላኳት የሰማይ መንኮራኩር ከመቶ ሚሊዮን ማይሎች በላይ ተጉዛ ፎቶግራፍ በመላኩዋ ምን ያህል እንዳደጉ ሲደነቁ ነበር። ነገር ግን ያ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር መፈጠሩን አላስተዋሉም። ይህ ዕድገትና እንቅስቃሴ በአደጉት አገሮች የሚካሄድ ሲሆን በእንፃሩ ደግሞ ለመኖር እንኳን የማይችሉ ሰዎች የሚኖሩበት ዓለም መሆኑን ስንመለከት የዓለም አዝማሚያ ወዴት እየሄደ እንደሆነ ለማስተዋል እስኪሳነን ድረስ እንገረማለን።

ይህ ድህነትና አለቃቂ የኑሮ ደረጃ ከደረሰባቸው ሕዝቦች አንዱ አገራችን ስለሆነች የአገራችንን ሁኔታ ከእግዚአብሔር ሚዛናዊ አሠራር ጋር በማያያዝ ብዙ ኢትዮጵያውያን እግዚአብሔር በኢትዮጵያውያን ላይ አንድ አድልዎ እንዳደረገባቸው ያስባሉ። ነገር ግን በዓለም በልዩ ልዩ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች፣ በእግዚአብሔር አሠራር የማበላለጥ ሁኔታ ኖሮ ሳይሆን፣ ሰዎች በራሳቸው ያመጡት ያስተሳሰብና የአሠራር ውጤት ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ የምትለይ አይደለችም። ችግሩ ከእግዚአብሔር የአሠራር ጉድለት ሳይሆን ሰዎች ሊያደርጉ የሚገባቸውን ያህል ባለማድረጋቸውና ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸው ነው፤ ይህ ሁኔታ ቀጥሎ እንደተመለከተው በወንጌላት ተንፀባርቋል።

በማቴዎስ ወንጌል 25፣ 1-26 የተጠቀሱት ሁለት ምሳሌዎች ለዚህ ነጥብ ትልቅ ማስረጃዎች ናቸው። ሁለቱ ምሳሌዎች በአምስት ሰነፍ ልጃገረዶችና በአምስት ልባም ልጃገረዶች እንዲሁም ደግሞ በሁለት ጠንካራ አገልጋዮችና በአንድ ሰነፍ አገልጋይ አማካይነት የተዋቀሩ ገጸ ባሕርያት ናቸው። ወንጌሉ፣

ሁለቱም ወገኖች የተለያዩበት የሥራ መስክ፣ የነበሩበት ቦታና ጊዜ፣ የተሰማቸውም ኃላፊነት አንድ ዓይነት ነው። ውጤቱ መሥራት ባልቻሉትና መሥራት በቻሉት መካከል ነው። መሥራት ሲባል ደግሞ የአቅምን ያህል መሥራት ስላልቻሉ ብቻ ነው።

በሙሽራ አጃቢነት የተጋበዙት ሰነፍ ልጃገረዶች የተጠሩበትን ዓላማ አለማወቃቸውና ጊዜ ካለፈ በኋላ ያደረጉትን ነገር በጊዜው አለማድረጋቸው ነው ወደ ሠርጉ ቤት እንዳይገቡ ያደረጋቸው። ያኛው ደግሞ በተሰጠው መክሊት የአቅሙን ማድረግ ሲገባው፣ ባለማድረጉ ያላደረገበትንም ምክንያት በሌላ ሰው በማስባሰቡ፣ እሥር ቤትና ጥርስ ማፋጨት ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። ይህ በዚህ ዘመን ላለን ሁሉ፣ ማለትም ከግለሰብ ተነስተን በቤተሰብ፣ በጎረቤትነትና በአገር ደረጃ ልናስብበት የሚገባ ወቢይ ጉዳይ ነው።

እነዚህ ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ባለማከናወናቸው ምክንያት ፍርድ ላይ የወደቁ ወገኖች የፈረደባቸውን አካል ትክክለኛ እንዳልሆነ ሀሜታና ስሞታ ማሰማታቸው አልቀረም። ነገር ግን በእግዚአብሔር አሠራር ወይም በዚህ ወንጌል አገላለፅ መሠረት የችግሩ (የፍርዱ) መንስኤዎች የራሳቸው የሥራ ውጤት እንጂ ከሌላ የመጣ እንዳልሆነ ነው። ይህ ለእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌ ሆኖ የቀረበ ትምህርት ዛሬ በዓለም ዙሪያ በድህነት በሚገኙት ሕዝቦችና እንዲሁም መሪዎቻቸው የሚደመጠው የሌሎችን ጨቋኝነት ባይነት ስሞታ ከርሀብና ከድህነት ሊያወጣ አይችልም።

ስለዚህ ጉዳይ ሳስብ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ጋር የተወያየሁት ትዝ አለኝ። በፕሮፌሰሩ ገለፃ መሠረት የአገራችን ጉዳይ ከእግዚአብሔር አሠራር ጋር ሳይሆን ከመንግሥት አስተዳደር ብልሹነት አኳያ የተፈጠረ ነው ይላሉ። ፕሮፌሰሩ እግዚአብሔር የኢትዮጵያን ድህ ገበረ የመቅጣትና የማስራብ ውሳኔ የለውም። መራቡና መቀጣቱ ከራሳችን አስተዳደር የመነጨ ነው ይላሉ። እኔም በመሠረቱ ሀሳቡ ተስማምቼ በኃጢአት ምክንያት ነው የምልበትን ለመግለፅ ሞክርኩኝ፤ ኃጢአት የምንለው ነገር

በሕግ ቋንቋ ወንጀል፣ በደል፣ በጠቅላላው ክፉ የተባለ ነገር ነው። አንድ መንግሥት ከእንደዚህ ዓይነት ውድቀት የሚደርሰው የጎሊና ዳኛ ወይም እምነት ስለሌለው ነው።

በክርስትና ቋንቋ እምነት የምንለው ጉዳይ፣ እግዚአብሔር አውነተኛ አሠራር ያለውና በሥራው የማይሳሳት፣ እኔ የምሠራውን አውነትና ሐሰትም በትክክል የሚያይ የበላይ ተቆጣጣሪ ነው ብሎ ማመን ነው። ይህን የማያደርግ ሰው ወይም አመራር የበላይ ተመልካችና ተቆጣጣሪ ስለማይኖረው አሁን በሀገራችን እየተደረጉ ያሉት አሰክ አሁን የተደረጉትን የጥፋት ውጤቶችን የሚሠራ መንግሥት ነው ማለት ነው፤ ይህ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት የሚለው። መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ስለሚል አሁን የምናደርጋቸው ነገሮች በሙሉ ወደ ሞት የሚያመሩ በመሆናቸው የኃጢአት ውጤቶች ናቸው ብለን አንደመድማለን ማለት ነው። ስለዚህ ይህን ሃሳብ በሚከተለው ማጠቃለያ አንደመድመዋለን።

እግዚአብሔር በሥራው የማይሳሳት፣ ታላቅና ፍጹም አምላክ ስለሆነ ለሱና ለክብሩ፣ ለሕጉና ለቃሉ የማይታዘዝ ሁሉ ሰነፍ ነው። የሰንፍና ውጤት ደግሞ ድህነት ነው።

የድህነት ውጤትም ሞት ነው። ሰነፍ ሰው በልቡ እግዚአብሔር የለም አለ (መዝሙር 52፣ 1)። ሰነፍ ሰው አግዚአብሔር የለም የሚለው በእግዚአብሔር የመታዘዝ አናም የሱን በሕይወት ሚዛን ላይ የበላይነት ያለው መሆኑን መቀበል ስለሚያቅተው ነው። ነገር ግን ሰው ያለውን ይበል አንጂ የእግዚአብሔርን የበላይነት ሊወስድ ወይም ሊቀንስ አይችልም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በሥራው ፍጹም ስለሆነ ።

በፍርዱና በማዳኑ ፍጹም መሆኑ

በዚህ ነጥብ ላይ ማብራሪያ ለመሰጠት በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፍርድ እውነተኛነት የሚገልጽ አንቀጽ ማግኘትና ማወቅ አስፈላጊና ተገቢ ነው። በዚህም መሠረት ስለ እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅነት ሰናነሣ ትዝ ሊለን የሚገባው ቃል ጻድቅ የሚለው ነው። ጻድቅ የሚለው ቃል እውነተኛ የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል። ስለሆነም እግዚአብሔር አውነተኛ ፈራጅ ነው እንላለን ማለት ነው።

የእግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ በድርድርና በውይይት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ማለትም አንድን እውነተኛ ፍርድ ለመፍረድ በሌላው ላይ ጭቆና አያደርግም፣ ወይም የአድልዎ ፍርድ አያከናውንም። ለማይወዱት የፈረደውን ትክክለኛ ፍርድ በሚወዱት ላይም ያንኑ ይፈርዳል። ለምሳሌ ተወዳጆቹ በአንድ ወቅት በእግዚአብሔር ተወደው ምህረት ከተደረገላቸው በኋላ ባልተወደዱት የታየውን የኃጢአት ሥራ ከሠሩ ልክ በዚያ ባልተወደደው የተሰጠው ፍርድ በእነሱም ይበየናል። ጻድቁ ጽድቅ ባደረገ ጊዜ እውነተኛ ፍርድ የተፈረደለትን ያህል እንደገና ያው ጻድቅ ኃጢአት ባደረገ ጊዜ ለኃጢአተኞች የሚደረገው ፍርድ ይደረግበታል። ትንቢተ ሕዝቅኤል ይህንን ሃሳብ በሚገባ ያብራራዋል። *"እውነትን ለማድረግ ፍርዱን ቢጠብቅ እርሱ ጻድቅ ነው። ፊጽሞ በሕይወት ይኖራል ይላል ጌታ እግዚአብሔር ... በአራጣ ቢያበድር ትርፎቻቸውንም ቢወስድ በእውኑ እሱ በሕይወት ይኖራልን? በሕይወት አይኖርም፣ ይህንን ርኩሰት ሁሉ አድርጓልና ፈጽሞ ይሞታል። ደሙም በላዩ ላይ ይሆናል፣" (ሕዝ.. 18፣ 9-13)።*

በዚህ ሃሳብ መሠረት በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ሰዎች አንድ ጊዜ ደህና ሆነው ሌላ ጊዜ መጥፎ ቢሆኑ ባደረጉት ልክ እውነተኛ ፍርድ ይሰጣቸዋል። እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ሲያወጣ የተጠቀመውን ፍርድ በዚያው ፈርያንን በቀጣበት

እውነተኛ ፍርድ እሥራኤላውያንንም እንደሚቀጣ አረጋግጧል። መጽሐፉ ኢያሱ ይሆንን ነገር እንዲህ አስፍሮታል። *"ኢያሱም ሕዝቡን እሱ ቅዱስ አምላክ ነውና እርሱም ቀናተኛ አምላክ ነውና እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉምI መተላለፋችሁንና ኃጢአታችሁን ይቅር አይልም። እግዚአብሔርን ትታችሁ እንግዶችን አማልክት ብታመልኩ መልካም ካደረገላችሁ በኋላ ተመልሶ ክፉ ነገር ያደርግባችኋልI ያጠፋችሁማል አላቸውI" (ኢያ. 24፣ 19-20)።* ይህም እግዚአብሔር እሥራኤልን በመልካም አይን ያየውን ያህል እነሱ ሲክዱ ደግሞ በክፉ አይን እንደሚያያቸውና ከኃጢአተኛ ጋር ተቻችሎ መኖር እንደማይችል ማረጋገጫ ነው።

ይህንኑ ነገር ሐዋሪያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ በተገቢ መልኩ አብራርቶታል። *"አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩI ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩI ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁI ሁሉም ያንን መንፈሳዊ መብል በሉI .... እግዚአብሔር ግን ከነሱ በሚበዙት ደስ አላለውምI በምድረ በዳ ወደቀዋልናI" (1ኛ ቆሮ. 10፣ 1-5)።* በዘዳግም እንደተገለጸው የእሥራኤል አመጸኛ ልብና አልመለስ ባይነት፣ ልክ እንደ አመፀኛው ፈርዖንና እንደ ተከታዮቹ ኤርትራ ባሕር እንደ ዋጠቻቸው ሁሉ እነዚህም የእግዚአብሔር ሕዝቦች የተባሉት በአመፅ ስለተሞሉ የሲና በረሀ ውጧቸዋል። ከዚያ ተርፈው ከተሰፋው አገር ከገቡና መንግሥትና ሥርዓተ አምልኮትም አቋቁመው በእግዚአብሔር ጥላ ሥር ከነበሩ በኋላም ያው አመፀኝነታቸው ስላለቀቃቸው እግዚአብሔር በነቢያቱ በኩል ፍርዱን ሲያስተላልፍ እንመለከታልን።

ገበሬ ለወይኑ መሬትና ለወይኑ የሚጨነቀውን ያህል ለሕዝቦቹ የተጨነቀው እግዚአብሔር ፍሬ ቢያጣባቸውና እውነተኝነት ባያገኝባቸው ጽድቅ በሆነው ፍርዱ እነሱንም አገራቸውንም እንዳጠፋ ማረጋገጥ ይቻላልI *(ኢሳ. 5፣ 3-8)።* ይህንን ሲያደርግም ልክ እነሱ በሠሩት የሥራ ውጤታቸው እንጂ

እግዚአብሔር ክፉ ሆኖ ወይም በፍርዱ እድልየ አድርጎባቸው እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል።

እግዚአብሔር ለማንም እያደላምI ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ነው። *"ክፉን በሚያደርግ ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታልI አስቀድሞ በአይሁዳዊ ዳግምም በግሪክ ሰው ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል። አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው እግዚአብሔር በለው ፊት እያዳላምናI" (ሮሜ 2፣ 9-11)።* እግዚአብሔር ለፍርዱ ምክንያት የለውምI የሱ እውነተኛ ፍርድ ለሱ፣ ከሱ፣ በሱ ስለሆነ በማንኛውም ሊደለል በየትኛውም ሊታለል አይችልም። ስዚህ ነብር ነቢያቱ ሁሉ በእሥራኤል ላይ የተደረገውን እውነተኛ ፍርድ ኃላፊነቱን መውሰድ ያለባት እራሷ እሥራኤል እንጂ እግዚአብሔር የተሳሳተ ፍርድ ፈርዶ እንዳልሆነ መልዕክታቸውን ያስተላለፉት።

እግዚአብሔር ሐዘኑን በእርምያስ በኩል ሲያስተላልፍ ይህንን የእሥራኤልን አመፀኝነት እንዲህ በማለት ነበር የገለፀውI *"ቀፎ ወፎችን እንደሚሞላ እንዲሁ ቤታችሁ ሸንገላን ሞልታለችI እንዲሁም ከብረዋልI ባለፀጎችም ያለ ልክ አብዝተዋልI የደሀ አደጎች ነገር መልካም እንዲሆን አልተሟሉላቸውምI የችግረኞችንም ፍርድ አልፈረዱላቸውም። በውኑ ስለነዚህ ነገሮች አልቀሰፍምን? ይላል እግዚአብሔርI ነፍሴስ በእንደዚህ ያለ ሕዝብ ላይ አትበቀልምን? ይላል እግዚአብሔርI" (ኤር. 5፡ 27-29)።* በዚህ በእሥራኤል ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር የወሰደውን እርምጃ ዳንኤል እውነትና ጽድቅ እንደሆነ መስክሯል። *"...ለአባቶቻችንም ለአገሩም ሕዝብ የተናገሩትን ባሪያዎችህን ነቢያትን አልሰማንምI። ጌታ ሆይI ጽድቅ ለአንተ ነው...I" (ዳን. 9፣ 6-7)።* አህምያም በበኩሉ ይህንን ነገር ያጸድቃል፡ *"....እኔና የአባቴ ቤት በድለናል። እኛም በአንተ ላይ እጅግ ክፉ ሠርተናልI" (ነህ. 1፣ 7)።* በዚህም ምክንያት ተሰደናል። ይህ ሁሉ ግን እኛ ባደረግነውና በአጠፋነው ስህተት እንጂ እንተ አድላዊ ፈራጅ ስለሆንክ አይደለም።

እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጠ የፈረደውን ፍርድ ኢሳይያስ እንዲህ በማለት አስቀምጠታል። *"ሂድ፣ ይህን ሕዝብ መስማቱን ትሰማላችሁ አታስተውሉምና፤ ማየትንም ታያላችሁ አትመለከቱምም በላቸው። በአይናቸው እንዳያዩ በጆሮዎቻው እንዳይሰሙ፣ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፣ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፣ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን፣ ጆሮዎቻውንም አደንቁር፣ አይናቸውንም ጨፍን አለኝ፤"* (ኢሳ. 6፣ 9-10)። ይህ እባባል አይቶና ሰምቶ ያልተመለሰውን ፈርዖንን እስኪጠፋ ድረስ በወደደውና በመረጠው ምርጫ እንዲቀጥልበት የማደንደን ፍርድ እንደፈረደው ሁሉ ያንኑ ተመሳሳይ በመረጣቸው ሕዝቦች ላይ ፈረደ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍርዱ ጽድቅና እውነተኛ ስለሆነ። በዚህም ምክንያት ሕዝቦች የሚኖሩባቸውን ቦታዎች እስኪያጡና ዘሮቻቸው ሁሉ እስኪነቀሉ ድረስ ፍርዱ መጽደቅ ነበረበት።

እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ ስለሆነ በሰው የዕለት ተዕለት ተግባር ሁሉ ያገባዋል። እግዚአብሔር ለአዋቂዎች በእውቀታቸው፣ ለሀብታሞች በሀብታቸው፣ ለባለሥልጣናቸውም በሥልጣናቸው ምክንያት ፍርድ አያዳላም። በዚህም አንባር ደግሞ የድሆቹን ጩኸት አይንቅምና በዚያ ፈንታ ለድሆቹ ያስባልና ይጨነቃል። በዚህም ምክንያት እውነተኛ ፍርድ ያደርግላቸዋል። እግዚአብሔር የሰዎች ከልብ ያልሆነ ጸሎትና ምጽዋት፣ ጾም እያስደስተውምና በዚያ ፈንታ ውስጣዊ ስሜትን የማይነካና እግዚአብሔርን የማያስደስት ጸሎትና ጾም ያስመርረዋልና *(ኤር. 14፣ 12፤ 18፣ 15-16)*።

ስለሆነም እግዚአብሔር በሕይወት ሚዛን ላይ የበላይና ተቆጣጣሪ ነው። በዚህ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር የበላይነት በደህንነት ሥራውም ፍጹም እውነተኛ ስለሆነ በማዳን ሥራው ላይ የሕይወታችን ሁሉ የበላይ ነው። ስለ እግዚአብሔር ማዳን ስናነሣ መጀመሪያ መዳን የሚያስፈልገውን የሰው ሕይወት ማየት አስፈላጊና ተገቢ ነው። ለዚህ ጉዳይ ትልቅ መረጃ የሚሆነን

የጳውሎስ ትምህርት ነው። ጳውሎስ ስለእግዚአብሔር ማዳን ሲጽፍ ጠቅላላውን የሰው ልጅ ሁኔታ በሱ ሕይወት መስሎ እንደገና ደግሞ የእግዚአብሔርን ቅድስናና የኃጢአትን አስጨናቂነት በሌላ በኩል አቁሞ ይመረምራል። ጳውሎስ መጀመሪያ ያየው፣ ሕግ በሰው ላይ የወሰነውን ፍርድ ነው። ሰው በሕግ ፊት ሲቆም ኃጢአተኛ ነው። ጽድቅ ለመሥራት ቢፈልግም ማድረግ አይችልምና፤ ስለዚህ ከውስጡ በሚፈልቅ ክፉ ነገር ገፋፊነት ሳይወድ በግዱ ክፋትን ይሠራል። ይህን የሚያደርገው ግን እሱ ፈልጎ ሳይሆን በውስጡ ያለው ኃጢአት ነው። ስለዚህ ከዚህ ሳይወድ በግድ ኃጢአት ከሚያሠራው ባላንጣ የሚያድነው ያስፈልገዋል። የሚያወጣና የሚያወርደው ከሌለ በዚያ ውስጥ ይኖራልና *(ሮሜ 7፣ 13-20)*።

በሌላ መልኩ ደግሞ እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ ይህንን እሱ በሠራው ሕግ ፊት ኃጢአተኛ የሆነን ፍጡር ከኃጢአቱ መቀበል አይችልም። ምክንያቱም እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ በመሆኑ። እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ መሆኑ የሚታወቀው ኃጢአት የጠየቀውን ዋጋ በመክፈልና እውነተኛ ፍርድ በመፍረድ ሰውን በማዳን ብቻ ነው። ስለሆነም ሐዋርያው ይህን ነገር እንዲህ በማለት ይገልጸዋል። *"እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለኛ ኃጢአት አደረገው፤"*(2ኛ ቆሮ. 5፣ 21)።

በዚህ ሃሳብ መሠረት የእግዚአብሔር ጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሰው በነፃ ተሰጠ። በሌላ አባባል ኃጢአት የጠየቀውን ደመወዝ ሞትን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመቀበልና የኃጢአትን ዕዳ በመክፈል የሰውን የራሱ አደረገ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር ተቻችሎ መኖር ስለማይችል ኃጢአትን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመቅጣት ጽድቅን ለሰው ሰጠ። ይህ አሠራሩ እግዚአብሔር እውነተኛ ፈራጅ እንደሆነ ማረጋገጫ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ትምህርት እግዚአብሔር ሰውን እዳነ ሲባል፣ እንዲሁ ሰውን ዝም ብሎ ከኃጢአቱ ተቀበለው ሳይሆን

ኃጢአት ሕግ የጠየቀውን ዋጋ ሙሉ በሙሉ በመክፈል ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር በሕይወት ሚዛን ላይ የበላይ ነው በሚል ነጥብ እንድንመለከት የተገደድነው።

ሲጠቃለል ከላይ ባየናቸው ሦስት ነጥቦች መሠረት ሰው በሁለንተናዊ መንገዱ በሕይወት ለመጓዝ ከፈለገ በገንዘብ፣ በሥልጣን ወይም በሌላ ኃይል ሥር ሳይሆን በእግዚአብሔር ሥር መሆን አለበት። የሕይወት ሚዛን ሳያጋድል ሊጓዝ የሚችለው በዚህ ሥርዓት ነውና።

ክፍል አምስት
<u>የሰው ድርሻ</u>

እስከ አሁን ያየነው በሰው ውድቀት ምክንያት ተያይዞ የመጣውን ኃጢአትና በኃጢአትም ምክንያት የሰው ልጅ የገጠመው የመከራ ጉዞ ምን እንደሚመስል ነበር።

በዚህም ምክንያት ሰው በደስታ ለመኖር ማድረግ ያለበትንና ያሰበውን ማድረግ ባለመቻሉ ከፍላጎትና ከምኞት አኳያ የገጠመውን ችግርም ተመልክተናል። በዚያው አኳያ ደግሞ የሕይወት ሁሉ የበላይ የሆነው እግዚአብሔር ለሰው የነበረውን እቅድ፣ በእቅዱም መሠረት ሰው ሊጓዝ ስላልቻለ ቅጣቱ ምን እንደሆነ ከመገንዘብ ጋር (ከቅጣት በኋላ) የእግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ ምን እንደሚመስል በተገቢ መልኩ ተመልክተናል። እንደዚህ ከሆነና በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት በእግዚአብሔር ብቻ የሚወሰንና ሰውም ከተደረገለት ውጭ ሌላ ማድረግ የማይችል ከሆነ፣ የሰው ድርሻ ምን ሊሆን ነው? ይህንስ ጉዳይ በዋና ርዕሰነት ለማብራራት ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ የሚሆነው ሰው በሰውነቱ ሊያደርገው የሚገባ ነገር ስላለ ነው ይሆናል። እነዚህም አራት ነገሮች ናቸው።

1. ሰው፣ ሰው መሆኑን ማወቅ፣
2. ኃጢአተኛ መሆኑን መገንዘብ፣
3. በራሱ መዳን የማይችልና ማመን እንደሚያስፈልገው ማወቅ፣
4. በአመነው መኖር እንደሚያስፈልገው መረዳት።

እነዚህ አራት ዐበይት ጉዳዮች ሰው ሊያደርጋቸው የሚገባው የሥራ ድርሻዎች ናቸው። እነዚህንም ቀጥሎ በየተራ እንመለከታቸዋለን።

ሰው፣ ሰው መሆኑን ማወቅ

አንድ ቀን አንድ ቦታ ላይ የማስታወቂያ ወረቀት ሳነብብ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎበታል። የምናስተምራችሁ የምታውቁትን እንድታውቁ ነውI እነዚህ ሰዎች ሊሉ የፈለጉትI ሰው ያወቀውን ካላወቀ ያላወቀውን ያውቃል ወይም የቀረውን ያውቃል ማለት ነው። በዚህም መሠረት ሰው መሆኑን ካወቀ ታላቅነቱንና ማንነቱን ስምንና እንዴት እንደተፈጠረ ያውቃል። መቸውም ቢሆን በዚህ ምድር ላይ ማንነቱን እንዲያውቅ የተረዳ ፍጡር ቢኖር ሰው ብቻ ነው። ሰው በዚህ ምድር ላይ እንዲኖር ብቻ ላይሆን እንዲጠብቅI እንዲገዛI አንዲንከባከብና አንዲነግሥበት የተፈጠረ መሆኑ የሚታወቀው በአፈጣጠሩ ልዩ መሆኑን ሲገነዘብ ነው።

ሰው በአፈጣጠሩ ልዩ መሆኑንIመጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ስለሰው አፈጣጠር በተለያየ መልክ ይነግረናል። *"እግዚአብሔርም አለI ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠርI" (ዘፍጥ. 1I 26)*። በዚህ ቃል መሠረት ሰው ከሌላው ፍጥረት ሁሉ የተለየ ነው። የተለየ የሚያደርገውም በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ በመፈጠሩ ነው። በሌሎች ፍጥረታት ቅደም ተከተልና አፈጣጠር ሥነ ሥርዓት የዚህ ዓይነት ቃል አናነብምI ይህንን ነገር የምናነበው በሰው አፈጣጠር ላይ ብቻ ነው። ስለሆነም ሰው እግዚአብሔርን መስሎ በእግዚአብሔር አርአያ መፈጠሩን ማወቅ አለበት።

እግዚአብሔር ሰውን እንፍጠር ሲል ማንነቱን በትክክል ገልጿል። እግዚአብሔር የብዙ ቁጥር በመጠቀም ሰውን ሲፈጥር አንድነትን በሦስትነት ወይም ሦስትነትን በአንድነት ያለው አምላክ መሆኑን ገልጿል። የዚህ ዓይነት ባሕርይ ያለው ሰው ነው። በአንድ አምላክነት ሦስት ኩነታትና አካላት ያለው አምላክI ነባቢት (ተናጋሪ) ለባዊና(አስተዋይና) ሕያዊት (ነዋሪት) ነፍስ ያለችው ሰው መፍጠሩን እንፍጠር በማለት አረጋገጠ። ሌላ ፍጥረት ይህንን አይመስልም። ሰው ብቻ እግዚአብሔርን መስሎና በአምላኩ ሆኖ በጥበብ ተፈጥሯል። ይህንን የማወቅ የሰው ታላቁ ድርሻው ነው።

ሰው በድንገተኛ ወይም በአጋጣሚ አልተፈጠረምI ለሥራI ለዓላማና ለእቅድ ተፈጥሯል። ቃሉ እንዲህ ይላልI *"...ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአትI ግዙአትም። የባሕርን አሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸውI" (ኦሪ. ዘፍጥ. 1I 28)I* በማለት ሁሉንም እንዲገዛI እንዲያስተዳድር የተፈጠረ ሲሆን በነሱም ደግሞ እንዲኖርና እንዲደሰት ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ሰው ሰውነቱን አንዲያውቅ ከሚያስገድዱት ነገሮች አንዱ ሕያው ነፍስ ያለው ሆኖ መፈጠሩ ነው። በሌሎች ፍጥረታት ሕያዋን ሆነው የመፈጠር ነገር ቢኖራቸውም በደመነፍስ ብቻ የሚኖሩ ሆነው ተፈጥረዋል። ሰው ግን ከእግዚአብሔር በተሰጠች ሕያዊትና ለባዊት ነፍስም እንድትኖረው ሆኖ መፈጠሩ ብቻ ላይሆን የአግዚአብሔር ምሳሌ መሆኑ ማረጋገጫው ነው።

ሌሎችን ፍጥረታት ስንመለከት መኖሪያ ቦታቸውና የአኗኗር ይዞታቸው የተጠቀሰው በጠቅላላ ነው። ሰው ግን ከተፈጠረ በኋላ የተወሰነ ቦታ የተሰጠውI ቦታውም የሚያስደስት እንደነበር መሆኑን ስናይ የሰውን ታላቅነት መረዳት እንችላለን።

ሰውI ሰው መሆኑ የሚታወቀውና ታላቁ ተፈጥሮአዊ ሥጠታው የሚታወቀው ክፉውንና መልካሙን ለይቶ ማወቁ ነው። ይህ ሃሳብ ሰው ክፉና በጎውን በማወቁ ምክንያት ለሚያካሂደው ማንኛውም ነገር ኃላፊነትና ተጠያቂነት አንዳለበት ነው። ይህም ሰው ነፃነት ከኃላፊነት ጋር እንደተሰጠው ያስረዳል። ለምሳሌ ብላ የተባለውን ያህል አትብላ የሚል በዚያው ልክ ኃላፊነት ከነፃነት ጋር ሲሰጠው እንመለከታለን። በዚህም ምክንያት ሰው ለሚያደርገው ማንኛውም ነገር ተጠያቂና ኃላፊ ስለሆነ ለሚመጣው ውድቀት ወይም ድህነት የመሸከም ግዴታ አለበት። ይህም የሆነበትን ምክንያት በሚቀጥሉት ሦስት ነጥቦች እንመልከት።

1. ምድርንና በውስጡ ያሉትን ሁሉ እንዲገዛ ሆነI

1. ያበጃትና ይንከባከባት ዘንድ እንዲችል ጌት የምትባል ቦታ ተሰጠችው፤
2. እንዳይሞትና ዘለዓለማዊ ሆኖ እንዲኖር ክፉና ደጉን የሚያሳውቀውን ዛፍ እንዳይበላ የሚከለክል ሕግ ተሰጠው።

እነዚህን ሦስት ነጥቦችን በሌላው ፍጥረታት አንመለከትበትም። እንዲያው በጠቅላላው በሰማይ የሚበሩ፣ በደረቅ (በየብስ) የሚጓዙ፣ በባሕር ውሰጥ የሚርመሰመሱ ጥቃቅንና ታላላቅ ፍጥረታት ሲፈጠሩ ከላይ ያልናቸውን ኃላፊነቶች እንዲያደርጉ አልታዘዙም፤ በተፈጥሮም አልተሰጣቸውም'። ሰው ግን የዚህ ሁሉ ኃላፊ ጌታ ንጉሥ ሆኖ ተፈጥሯል። መጽሐፍ ቅዱስ ማንነቱን እንዲህ ነው የሚገልፀው።

እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፤ አሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንሰሳትንም፣ ምድርን ሁሉ በምድር የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዛ በማለት የሰውን ጌትነትና ታላቅነት ይገልጻል። ሰው አዋቂ በመሆኑ በአውቀቱ ተጠቅሞ የሚያስተዳድራቸውን እንሰሳት በመልካቸውና በግብራቸው ከማወቁም በላይ በዚያው በአወቀው መጠን ስም የማውጣትና የመጥራት ኃላፊነት ከእግዚአብሔር ሲሰጠው እንመለከታለን። *"እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ፤ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው፤ አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደጠራው ስሙ ያው ሆነ፤"* (ዘፍጥ. 2፣ 19)። የሰውን አዋቂነትና ለባዊነት የሚያረጋግጠው ይህ ነው። ሰለዚህ ሰው፣ ሰው መሆኑን በዚህ መረዳት አለበት።

<u>ኃጢአተኛ መሆኑን መግንዘብ</u>

ከዚህ በላይ ያየነው ሃሳብ የሚያሰረዳን የሰውን አዋቂነትና ታላቅነት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሰው መልካም ኑሮን ይኖር እንደነበር መረዳት ችለናል። ያም ሆኖ ግን አሁን ሰው ላለበት ሁኔታ ከላይ ያየነው ዓይነት እንዳልሆነ መረዳት እንችላለን። ሰለሆነም በሰው ሕይወት ውሰጥ ችግር አለ ማለት ነው። ያ

ችግርም ኃጢአት መሆኑን ከዚሁ መጽሐፍ በሁለተኛው ምዕራፍ ተገንዝበናል። ሰለዚህ ይህ ኃጢአት ምን እንደሆነ ሰው መረዳት አለበት። ከዚህ በላይ በዘረዘርነው መሠረት የሰው ትልቁ ችግር በሰህተቱ ኃላፊነትን አለመውሰድና ለተሳሳተው ሰህተት ይቅርታ አለመጠየቅ ነው። በሃይማኖት ትምህርት ግን ትልቁ ሰው ላደረገው ሰህተት ኃላፊነትን ወስዶ ይቅርታ መጠየቅ ነው፤ ነገር ግን ይቅርታ ጠያቂው ይቅርታ የሚጠይቅበትን ምክንያት ካልተረዳና ካልገባው ይቅርታ መጠየቅ ራሱ ትርጉም የለሽ ይሆናል።

በዓለም ሕግ ይቅርታ የሚያስጠይቁ ወይም ለይቅርታ የሚጋብዙ ጉዳዮች ከጎበረተሰቡ አኳያ እንዲሁም ጎብረተሰቡ በሚኖረው የኑሮ ሕግ መሠረት መሄድ ያልቻለ (ሕግ የጣሰ) ሰው የሚጠየቀው ጉዳይ ነው። ሰው አዋቂና ከፍጥረት በላይ ሆኖ መፈጠሩ የተመደበለትን ኃላፊነት በትክክል እንዲወጣ ነበር። ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ምክንያት ጎሊናን የሚሰብርና አእምሮን የሚነካ ፀፀት ይሰማዋል። ለዚህም ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት የጎሊና ሕግ ያስገድደዋል። በመሆኑም ሰው ከላይ ባየነው የተፈጥሮ ብቁነት ምክንያት ያደረገው ነገር ሰህተት መሆኑን እንዲያውቅ አድርጎታል፤ *(ዘፍጥ. 3፣ 1-13)*።

ከላይ የተገለጸው ሰው በደለኛ መሆኑንና በደል የተሰማው መሆኑን ያረጋግጣል። የአዳምና የሔዋን ልጅ የሆነው ቃየል አታድርግ እየተባለ ባደረገው ነገር ተፀፅቶ አልቅሶ ይቅርታ ሲጠይቅ እንመለከታለን፤ *"ኃጢአቴ ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት፤ እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሰደደከኝ፤ ከፊትህም እሰወራለሁ፣ በምድርም ኮብላይና ተቀበዝባዥ እሆናለሁ፣ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገለኛል፤"* *(ዘፍጥ.4፣ 13)*።

ይህ ሃሳብ ቃየል በፊት ኃጢአት ሳያደርግ የነበረው ሰው አይደለም። ወንድሙን ከገደለ በኋላ ሲለቃይ የኃጢአት ሰሜትም ተጠያቂነትንና በደለኝነትን እንዲሰማው ሲሆን እንመለከታለን። በዚህ በደለኝነቱና ሕግ ተላላፊነቱ ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት ያምናል። ለዚህ ነው ኃጢአቴ ልሸከማት የምችላት አይደለችም፤

ሌላው ቀርቶ የምረገጣት ምድር እንኳን እኔን መሸከም ስለማትችል በደሌና ኃጢአቴ ለምድር ስለሚከብድ አንድ ቦታ መቆም የማልችል ኮብላይና ተቀብዝባዥ እሆናለሁ። የአንተን የእውነተኛውን ፊት ለማየት ስለማልችል ከምድር ሁሉ አሳደድከኝ። ስህተቴ ነው ፍርዱን ተቀብያለሁ፤ ነገር ግን ስህተቴ የጠየቀውን ዋጋ መክፈል አልችልም። ከአንተ ምሕረት እሻለሁ ይላል። ይህ በስህተቱ ያመነና ይቅርታ የጠየቀ ሰው ከእግዚአብሔር ምህረት ማግኘት እንዳለበት ያውቃል። *"እግዚአብሔርም እርሱን አለው እንግዲህ ቃየልን የገደለ ሁሉ ሰባት እጥፍ ይጠየቅበታል። እግዚአብሔርም ቃየልን ያገኘ ሁሉ እንዳይገድለው ምልክት አደረገበት፤" (ዘፍጥ. 4፤ 15)።*

ይህ ሃሳብ የሚያስተምረን ሰው ኃጢአተኛነቱና በደለኝነቱ ምን ያህል ክፉ ቢሆንም ከእግዚአብሔር ምህረትን ካገኘ መዳን እንደሚችል ነው። ኃጢአት ሁል ጊዜ ዋጋ ይጠይቃል። የኃጢአት ዋጋ ሞት ስለሆነ ሰው ካልሞተ በቀር የኃጢአት ደመወዝ አይከፈለውም፤ (ሮሜ 6፤ 6)። ሆኖም ግን ኃጢአተኝነትን አለማመንና በኃጢአት ውስጥ መሆንን አለመረዳት ሌላው ኃጢአተኝነት ነው። ኃጢአተኝነትና በደለኝነት የማይሰማው ሰው ክፉ ይባላል። እንደዚህ ያለ ፈርያናዊ ልብ ያለው ሰው እውነትን የማይወድና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን የሚመርጥ ይሆናል፤ *"ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና። ሥራው እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም። እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆን ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል፤" (ዮሐ. 3፤ 20)።*

ከዚህ ሃሳብ በአጠቃላይ የምንረዳው፣ ሰው ኃጢአተኝነቱን ከተረዳ ምህረትን መጠየቅ እንዳለበት የማወቅ ኃይል እንዳለው ነው። ይህ ሲባል ግን ሰው በራሱ የኃጢአትን ዋጋ ከፍሎ ከኃጢአት ነፃ ይሆናል ማለት አይደለም። የሰው ድርሻ ኃጢአተኝነትን መረዳት ብቻ ነው። *"እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ፤ ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?" (ሮሜ 7፤ 24)።* የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ ሰው በኃጢአት ውስጥ እንደሆነና ኃጢአትም

ምን ያህል ከባድ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው። ሐዋርያው የሚያስተምረን ኃጢአትንና በኃጢአት ምክንያት የመጣውን ሞት በውርስ ኃጢአት የተያዘ ሰው ብቻውን ሊወጣው እንደማይችል ነው። ይህ ማለት ግን የኃጢአት መርዛማነትና ክፋት አልተሰማውም ማለት አይደለም። ሰው ኃጢአተኝነት በስተሰማውና ኃጢአት የጠየቀውን እዳ ከፍሎ መውጣት ስላልቻለ ና አድነን በማለት ይጮሃል፤ *(መዝ. 143፤ 7፤ 42፤ 3)።*

ይህ የሚያስረዳን ሰው ኃጢአተኝነቱ እንደተሰማውና ለዚያ ለተሰማው ኃይለኛ ጠላትም አዳኝ እንደሚያስፈልገው ተገንዝቧል። ነገር ግን ከዚያ ጭንቀት የሚያድነውን አሁንም በመጠባበቅ ላይ ነው።

ማመን እንደሚያስፈልገው መረዳት ማወቅ

ከዚህ በላይ ባየነው መሠረት ሰው ኃጢአት በመሥራቱ ምክንያት በደለኛና ኃጢአተኛ መሆኑን እንዲቀበልና ኃላፊነት እንዲሰማው ተፈጥሮአዊ ግዴታው መሆኑንና ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ ምክንያት የተፈረደበት መሆኑን ተረድተናል። ለዚህ መልስ የሚሆነን፣ እግዚአብሔር ከራሱ ፍቅር ተነስቶ በራሱ መዳን ያልቻለውን ሰውን ለማዳን ወሰነ። ይህ ውሳኔ ለሰው ደህንነት መስጠቱንና ያንን ነፃ ሥጦታም ሰው በእምነት መቀበል እንዳለበት ስለደህንነት የሚያስተምረው የእግዚአብሔር የማዳን ዶክተሪን ያስረዳል።

ይህ የደህንነት ሥጦታ ግን እግዚአብሔር ከራሱ ፍቅር በመነሣት ያዘጋጀው ሰው ለተባለ ፍጡር ሁሉ እንጂ ለተለዩና ለተመረጡ ሰዎች ብቻ እንዳልሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። የዮሐንስ ወንጌል የሚከተለውን ያስተምረናል፣ *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ*

ወዶታልI" (ዮሐ. 3I 16)። ይህ ሃሳብ የሚያስረዳን ለሚያምኑ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንደተዘጋጀ ነው። ይህም ከሰው ፍላጎት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ፍቅር በመነሣት እግዚአብሔር እንዲሁ ዓለሙን ስለወደደ ብቻ ስለሆነ ፍቅሩንም የገለጸው አንድ ልጁን በመስጠት ነው። የልጁ መሰጠት ምክንያትም፣ በልጁ መሰጠት ያመኑትም እንዲድኑ፣ የማመን አፀፋ መስጠት ያልቻሉት እንደሚፈረድባቸው ቃሉ እንዲህ ይላል። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ ወደ ዓለም አላከውምና *"በርሱ በሚያምን አይፈረድበትምI በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስለአላመነ አሁን ተፈርዶበታልI" (ዮሐ. 3I 17)።*

በዚህኛው ሃሳብ ደግሞ የምንረዳው ከእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር የተነሣ በተሰጠው ያለመነ፣ ካለመነበት ለዓት ጀምሮ ተፈርዶበታል። ይህ ሃሳብ የሚነግረን ስላልተመረጠ ሳይሆን መዳን ያልቻሰው ስላላመነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ይበል እንጂ በአሁኑ ጊዜ በተለይም የካልቪንን ተሐድሶ እንቅስቃሴ የሚያካሂዱ ፕሮቴስታንቶች ሃሳብ መሠረት ሰመዳን መመረጥ ያስፈልጋል ይሉናል። በፕሮቴስታንቶች ሃሳብ መሠረት አንድ ሰው ለማመንም መመረጥ አለበት። እግዚአብሔር ሊያድናቸው የፈለጋቸውን ቀድሞውኑ ስለመረጣቸው ከውስጣቸው የማመን ኃይል የላቸውም። ለማመንና የመንግሥተ ሰማያት አባል ለመሆን በእግዚአብሔር መመረጥ ያስፈልጋል ይላሉ። ከሚጠቀሙባቸው ጥቅሶች የዮሐንስ ወንጌል *(ዮሐ. 6I 44) "የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደኔ ሊመጣ የሚችል የለምI እኔም በመጨረሻው ቃል አስነሣዋለሁ"* የሚሰውና ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የጳውሎስ መልዕክት *(ሮሜ. 11I 18)* ከዳዊት መዝሙር የተጠቀሰውን ጻድቅ የለም አንድስ እንኳን አስተዋይ የለም ... የሰላምን መንገድ አያውቁም። በአይኖቻቸው ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም የሚሉትን ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳቦችን ይዞ በመነሣት ነው። እነዚህን ሃሳቦች በጥንቃቄ ብናያቸውና ብናስተውላቸው እነዚህ ሰዎች ከሚያብራሩት በፍጹም የተለዩ ናቸው።

የመጀመሪያውን ሃሳብ በዮሐንስ ወንጌል ያለውን ብንመለከተው ከላይ ለተጠቀሰው ሃሳብ ቁልፍ የሆነውን ሃሳብ እናገኘዋለንI እሱም *"ልጁን አይቶ በሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው። እኔም በመጨረሻው አስነሣዋለሁI" (ዮሐ. 6I 35-40)።* ይህንን በመስማታቸው ምክንያት አይሁድ አንጎራጎሩ ይላል። የማንጎራጎራቸው ምንጭም ከሀደት ነው። የእግዚአብሔር ልጅነቱን መቀበል ስላልፈለጉ የእግዚአብሔርንም የማዳን ሥራ በኢየሱስ ከርስቶስ በኩል መሆኑን አላመኑም። አሰማመን ብቻም ሳይሆን፣ እናቱንና አባቱን የምናውቃቸው የዮሴፍ ልጅ እንዴት ከሰማይ ወረድኩ ይለናል? ብለው ተቃወሙ። የላከው አብ እውነተኛ አምላክ እንደሆነና የአብ የማዳን መንገድም የላከው ወልድ ብቻ መሆኑን ስላልተቀበሉ አብ ያዘጋጀውን መንገድ ያልተቀበለ ሁሉ በዚያ መንገድ መምጣት እንደማይችል አረጋገጠ፣ እንጂ የተመረጡት ብቻ ይድናሉ ለማለት አይደለም።

ሁለተኛው ሃሳብም፣ የትምህርቱ መሠረታዊ አቋም በያዘው በሕግ እንፀድቃለን በሚሉት አይሁድና በእምነት እንፀድቃለን በሚሉት አሕዛብ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት እንደሌለ የተሰጠ እንጂ፣ ሰው በሰውነቱ ያለማመን ኃላፊነት የለውም ለማለት አይደለም። ሐዋርያው እያስተማረን ያለው ያን ጊዜ ላሉት አይሁድም ሆነ አሁን ለምንኖረው ክርስቲያኖች ሕግ ያፀድቃል ብላችሁ እንደሆነ በሕግ የፀደቀ የለም። በሕግ መፅደቅ የማይቻለውም ሕግ የኃጢአቱን ዋጋ መክፈል ስለማይችል ነው። ስለዚህ ሕግ የሌላቸው አሕዛብም ሕግ ያላቸው አይሁድም በእግዚአብሔር ዐይን አንድ ናቸው። በኃጢአተኝነት ደረጃ ለመዳን ግን ማመን አለባቸውI ካለመኑ ራሳቸውን ማዳን እንደማይችሉ የሚያረጋግጥ ትምህርት ነው።

ትክክለኛ አስተምህሮ መልዕክቱ ከላይ የተገለጠው ሲሆንI የፕሮቴስታንቱ ዓለም እንደሚለው ለመዳን መመረጥ የሚያስፈልግ ከሆነ የግኖስቲክ ራስን ከሌሎቹ የመለየትና እኔ ብቻ ነኝ የምፀድቅ የሚለውን የክህደት ትምህርት የሚያንፀባርቅ ነው። በፕሮቴስታንቱ

ዓለም ሞቅ ሲል ስሜታቸውን የሚቀሰቅስ፣ ባፈለጋቸው ጊዜ ደግሞ ስሜታቸውን የሚጥል ትምህርት ማስተማር የተለመደ ነው። ፕሮቴስታንት ሁል ጊዜ ለራሳቸው ትልቅ መቁረስ ስለሚፈልጉ እግዚአብሔር በምህረቱ የሰጠውን የማዳን ሥራ በነሱ ቲዮሎጂ ገደብ ሊሰጡ ይፈልጋሉ። ሊሉን የሚፈልጉት እግዚአብሔር መጀመሪያውኑ ሰዎችን ስለመረጠ ለማመንም ራሱ ካልተመረጥኩ በቀር መዳን አልችልም፤ በመሆኑም እግዚአብሔር እኔን ስለመረጠ ሌሎቹን አልመረጠም ወደሚለትና ቀድሞ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ተወግዙ የወጣውን የግኖስቲክ በፍጥረት መካከል መበላለጥ አለ፤ የሚለውን ፍልስፍና የሚያስረዳ ነው።

ፕሮቴስታንቶች ለእነሱ ሃሳብ ካልተስማማ የእግዚአብሔርን ቃል ላለመቀበል የሚያማኝ ነገር የለም። ፕሮቴስታንቱ ዓለም በአባትነቱ የሚመጻደቅበት ሉተር የሱን ሃሳብ ስላልተስማሙለት የያዕቆብን መልእክትና የዮሐንስን ራዕይ ክዱቸዋል። የክህደቱ መነሻ ለእኔ የሚጥም ነገር አላገኘሁበትም የሚል ነው። ለዚህ ነው ላለማመንም ተጠያቂነት የለብንም ለማለት የሚዳዳቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሰው በራሱ አይድንም፤ አለ አንጂ በክርስቶስ ለመዳን የማመን ኃይል የለውም አላለም።

አንድ ሰው በሽተኛ ከሆነና በሽተኝነቱን ካወቀ ለበሽታው መድኃኒት ይፈልጋል። ነገር ግን በሽታውን ያላወቀ ሰው ቢታመምና ቢያውቅ እንኳን ለበሽተኛነቱ እውቅና ካልሰጠ፤ የአእምሮ ችግር አለበት ይባላል። እርግጥ ነው ያ ሰው በሽተኛነቱን ላለመናገር ራሱ ይካድ እንጂ በሽተኛነቱን መካዱ ራሱ በሽታ መሆኑን በዚህ ጉዳይ ላይ ያጠኑ ሰዎች ይናገራሉ። ስለዚህ ሰው ማወቅ ያለበትና ኃላፊነቱም በራሱ መዳን እንደማይችል ተገንዝቦ ከእግዚአብሔር ምሕረትን መጠየቅ ነው። ይህንን ለማድረግም እውቀት ተሰጥቶታል። ይህ ሰው እውቀት የለውም ብሎ መናገር እግዚአብሔር እውነተኛ ፈጣሪነትና ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው መሆኑን መቃወም ነው።

በአመነው መኖር እንዳለበት መረዳት

እስከ አሁን ያየነው፣ ሰው፣ ሰው በመሆኑ ምክንያት ተፈጥሮአዊ ባሕርይውን ማወቅና ምን ያህል በእግዚአብሔር እንደተወደደ፣ በእግዚአብሔር መወደዱም ዋጋ እንደተከፈለለት ተመልክተናል። የዋጋው መጠንም የእግዚአብሔር አንድ ልጁ ብቻ መሆኑን ተገንዝበናል። ይህንን የእግዚአብሔርን አንድ ልጅ በዋጋ የተቀበለ ሰው ከኖረበት አዘቅት ወጥቶ የልጁ መንፈስ በሱ ስላለ እግዚአብሔርን አባቴ ብሎ እስኪጠራ ድረስ ድፍረት እንዲኖረው አድርጎታል *(ገላ. 4፣ 4-6)*።

ይህ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ እንዲጠራ ያደረገው መብትም እንዴት እንደሚኖር ዋጋ ይጠይቀዋል። ዋጋውም የቅድስና ኑሮ እንዲኖር ነው። ምክንያቱም በዓለም ካለው ይልቅ በነሱ ያለው ስለሚበልጥ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፤ *"እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። መብራትንም አብርተው ከእንቅብ በታች አይደለም እንጅ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል። በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል። መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ፤"* *(ማቴ. 5፣ 14-16)*።

ይህ ሃሳብ የሚያስረዳን በደሙ የተዋጁት፣ በፀጋው የተጠሩት፣ ዋጋ የተከፈለላቸውና የእግዚአብሔር የመንግሥቱ ካህናት የሆኑት ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው የሚያረጋግጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፤ *"በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደተመረጠና ክቡር ወደሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ፣ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሰዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ፤"* *(1ኛ ጴጥ. 2፣ 4-5)*።

የእግዚአብሔር ቃል ደሙ ስለፈሰሳቸው፣ በዋጋ ስለተገዙት ልጆቹ ምን መሆን እንዳለባቸው ብዙ የሚነግረን አለው። *"እናንተ ግን ከጨለማ ወደ እሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ። እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁምI አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁI እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁምI አሁን ግን ምሕረት አግኝታችኋልI" (1ኛ ጴጥሮስ 2፣ 9-10)።*

ሰው ክቡር ነበርI ወደቀI ነገር ግን አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝቶ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነI ከምንጊዜውም የበለጠ በአኗኗሩ የእግዚአብሔርን ክብር ማሳየት አለበት። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በዚህ ምድር ሲመላለስ ማዳንን፣ ዋጋ ከፍሎ ማከናወን ብቻ ሳይሆን ኑሮንም እንዴት እንደምንኖር አሰተምሮናል።

ታላላቆቹ ፍርድ ያደሉባቸውን እውነተኛ ፍርድ በመስጠት፣ ከወገን እርቀው በበሽታ የወደቁትን ለአንዴና ለመጨረሻ በመፈወስI *(ዮሐ. 5፣ 2-9)*። ዐይነ ሥውሮቹንና ዓለም የጨለመባቸውን ውስጣዊና ውጫዊ እውርነታቸውን በማስወገድI *(ዮሐ. 9፣ 1-12)*። ብቸኞቹን የሚያነጋግራቸው ያጡትን ድካማቸውን ደክሞ በማነጋገርና ችግራቸውን በመረዳትI *(ዮሐ. 4፣ 1-15)*። ለአባቱ ፍጹም በመታዘዝ ራሱን አስክ መስዋዕት አድርሶ የመስቀል ሞትን ሞቶ፣ ለእኛ ኃጢአት ሆኖ በመሰጠት ያከናወናቸው ድርጊቶች በሙሉ የዚህ ሁሉ መከራ ውጤት የሆነው ደህንነት የተከናወላቸው ሰዎች አንዲያደርጉትና እንዲኖሩት የተሰጠ የሥራ ድርሻ ነው።

መንፈሳውያን ስለሆንን በመንፈስ የመኖር ግዴታ አለብን። በእግዚአብሔር ስለተወደድንና የእግዚአብሔር ፍቅር ስለበዛልን መበርታት አንጂ መድከም እንደሌለብን የመንፈስ ነፃነታችንን በአግባቡ እንድንጠቀም የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል። *"ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ በባሕርያቸው አማልክት*

ለማይሆኑ ባርያዎች ሆናችሁ ተገዛችሁI አሁን ግን እግዚአብሔርን ስታውቁ ይልቅስ በእግዚአብሔር ስትታወቁ እንደገና ወደ ደካማ ወደ እሚናቅም ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ?" (ገላ. 4፣ 8-9)።

ባጠቃላይ ሰው፣ ሰው በመሆኑ ምክንያት ሰውነቱን ማለትም ሰው መሆኑን ከመረዳት አልፎ ኃጢአተኝነቱን፣ በኃጢአት ምክንያት ራሱን ማዳን የማይችል ሆኖ ዋጋ የተከፈለለት መሆኑን መረዳት አለበት። የተከፈለለት ዋጋ መጠንም የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ሲሆን የከፍያው መንስዔም የእግዚአብሔር ብዙ ፍቅር ሲሆንI ዋጋ የተከፈለለትና ነፃነት የታወጀለት የሰው ልጅ ደግሞ የኑሮ ይዘቱና ሕይወቱ ምን መሆን እንዳለበት የሰው ድርሻዎች መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

መደምደሚያ

"የሕይወት ሚዛን" ተብሎ የተሰየመው መጽሐፍ የሚያመለክተው መሠአታዊ ነጥብ የሰው ሕይወት በሚዛን ላይ ስመዘን ምን ይመስላል ማለት ነው። በዚህ ሃሳብ መሠረት መዛኙ እግዚአብሔር ሲሆን መመዘኛ መሣሪያው ደግሞ ቃሉ ነው። ይህ መሆኑን ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ ዝርዝር ማብራሪያ ውስጥ እንደተገነዘብን መረዳት እንችላለን።

አሁን በዚህ የመደምደሚያ ሃሳብ ላይ የምናጠቃልለው እግዚአብሔር ስለሚዛን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጠውን ነው። *"በፍርድ በመለካትም፣ በመመዘንም፣ በመስፈርም አመፅ አታድርጉ የእውነትም ሚዛን የእውነትም መመዘኛ ... ሁሉ ጠብቁ፣ አድርጉም፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።"* ዘሌ. 19፣ 35-37።

በዚህ ሃሳብ መሠረት የእግዚአብሔር ሰዎች በሚሠሩት በማንኛውም ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊና የሰብአዊ አሠራር እንዲጠነቀቁና እራሳቸውን እንዲመዝኑ ማረጋጫ ነው። በትንቢተ ሕዝቅኤል እግዚአብሔር አንዲህ ይላል። *"የእሥራኤል አለቆች ሆይ ይብቃችሁ፣ ግፍንና ብዝበዛን አስወግዱ። ፍርድንና ጽድቅንም አድርጉ፣ ቅሚያችሁን ከሕዝቤ ላይ አርቁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። እውነተኛ ሚዛን ... ይሁንላችሁ።"* 45፣ 9-12። ከዚህም የምንረዳው ሚዛን መሠረታዊ ይኑሮና የሕይወት መለኪያ መሆኑን ነው።

የዚሁ መሠረተ ሃሳብ ተመሳሳይ የምጽሐፍ ቅዱስ ቃል በትንቢተ አሞጽ ላይ እንደሚከተለው ይነበባል። *"ችግረኛውን የምትውጡ፣ የአገሩን ደሀ የምታጠፉ፣ እናንተ ሆይ እህልን እንሸጥ ዘንድ መባቻው መቼ ያልፋል? የኢፍ መስፈሪያውንም እያሳነስን፣ ሰቅሉንም እያበዛን በሃሰተኛም ሚዛን እያታለልን ደሀውን በብር ችግረኛውንም በአንድ ጥንድ ጫማ እንገዛ ዘንድ ... የምትሉ እናንተ ሆይ ይህን ስሙ።* እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር እንዲህ

ብሎ ምሏል። ሥራቸውን ሁሉ ለዘለዓለም ምንም እልረሳም። በውኑ ምድሪቱ ስለዚህ ነገር አትናወጥም ምን? ... ዝማሬያችሁንም ወደ ዋይታ እለውጠዋለሁ፣ ማቅንም በወገብ ሁሉ፣ ራሰ መንጨትንም በሁሉ ላይ አመጣለሁ፣ እንደ አንድያ ልጅም ልቅሶ ፍጻሜውንም እንደመራራ ቀን አደርገዋለሁ።" አሞ. 8፣ 5-10።

በጠቅላላ ከዚህ በላይ ያየነው ሰው በዚህ ምድር ላይ ሲኖር እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ትእዛዝ ሰጥቶት ያን ትእዛዝ በማዛባት ሌሎችን እየበደለ የኖረበትን የሕይወት ምስቅልቅል ነው።

በትንቢተ ዳንኤል 5፣ 27 ላይ "የነገሩ ፍቺ ይህ ነው፣ ማኒ ማለት እግዚአብሔር መንግሥትህን ቆረጠው፣ ፈጸመውም ማለት ነው። *ቴቄል* ማለት ሚዛን ተመዘነህ ቀልለህም ተገኘህ ማለት ነው።" አንግዲህ መዛኝ እግዚአብሔር አራሱ ሲሆን በመመዘኛው በቃሉ ተመዝነው ካላለፉ፣ ሰዎች ቀለሉ ይባላል።

በዚህ መጽሐፍም ከመጀመሪያ አስከ መጨረሻ የተመለከትነው የእግዚአብሔርን ቅድስናና ሰዎች ኃጢአት በመሥራታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ከተለዩ በኋላ በሕይወት ውስጥ የመጣውን ውጣ ውረድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናየው ለሰው ሕይወት የማይስማማ፣ ነገር ግን ሰው በግድም ሆነ በውድ እያደርገ ያለውን ስህተት ነው። ስለዚህ ከዚህ አበቸጋሪና ምስቅልቅል ሕይወት ለመውጣት በዚህ ጽሑፍ ከተገለፀውና የሕይወት ምንጭ ከሆነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ከመሆን ሌላ ምንም ዓይነት መፍትሔ እንደሌለ ነው።

ዘመናችን ከመስልጠኑ የተነሣ ለሰው ልጅ ዕድገትና እውቀት ብዙ ዕድል የሰጠውን ያህል በዚያው ልክ ደግሞ ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ሰፊና ብዙ ነው። ሰው በየደረሰበት ሁሉ መልካም ለማግኘት ዕድል ያለውን ያህል የመጥፎው አጋጣሚው በአጥፍ ይበዛል።

ከዚህ የተነሣ ከሞትና ከክፉ ለማምለጥ የሰው ልጅ ቀን ከሌሊት ሲዋትት ይታያል። ነገር ግን የዋተተውን ያህል የልብ እርካታ ሳያገኝ ደረቅ ሕይወትን እየመራ ይገኛል። ስለዚህ ይህ "የሕይወት ሚዛን" የሚለው መጽሐፍ መጠነኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል ተብሎ ስለታመነ፣ በአጠቃላይ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መቆም እንዳለበትና ደስታ ለማግኘትም ብዙ መዋተት እንደማያስፈልገው ይሞክራል። ከአሁን ቀደም የነበሩት ሰዎች ደስታ ለማግኘት ምን ያህል እንደሮጡ፣ ነገር ግን ከንቱና ነፋስ እንደመጨበጥ እንደሆነባቸው ተገንዝበናል። ስለዚህ፣ እነሱ በሮጡበትና ትርፍ ባላገኙበት መንገድ ዛሬ እኛ መሮጥ የለብንም። አሩጫና ድካም ከሮጥንና ከደከምን ትርፍና በረከት በሚያስገኘው በእግዚአብሔር ጥላ ሥር እንሩጥ።

በመጽሐፉ ውስጥ የተዘረዘረው ማንኛውንም ክፍል ለመተቸት ወይም ደግሞ ሌላኛውን ክፍል ከጥፋት ነፃ ለማውጣት ሳይሆን ስህተትም ሆነ ትክክል የተሠራው ሥራ ሁላችንንም የሚመለከት መሆኑን ተገንዝበን እንድንማርበት ነው።

ከምንጊዜውም በላይ ራሳችንን የምናይበትና ስህተታችንን የምንመረምርበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። ያም ደግሞ እንደመስተዋት ሆኖ ራሳችንን ሊያሳየን የሚችለው በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ ስንኖር ብቻ ነው። ጥበበኛውም ደስታን ፈልጎ ያገኘው ከዚያ ነውና። አንተ ግን እግዚአብሔርን ፍራ፤ ትዕዛዙንም ጠብቅ፤ ክፉም ቢሆን በጎም ቢሆን እርሱ ሁሉንም ወደ ፍርድ ያመጣዋልና ከብርና ምስጋና ለአምላካችን ይሁን።

ዋቢ መጻሕፍት

በአባ መልከጼዴቅ (ሊቀ ጳጳስ)፣ የቋሚ ምስክርነት፣ ዓለም ማተሚያ ቤት Danville, CA 1995.

መድኃኔ ታደሰ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ጦርነት (የግጭቱ መነሻና መድረሻ)፤ 1992፣ ብ. ሰ. ማ. ድ.

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አርዓያ እና መዝገቡ ምትኬ ቢልልኝ፣ ጥርስ የገባች ሀገር፣ (ትርጉም) ጎዳር 1986.

ተስፋዬ መኮንን፣ ይድረስ ለባለ ታሪኩ፣ ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ጥቅምት 1985 ዓ. ም.

ዘውዴ ረታ፣ የኤርትራ ጉዳይ፣ ሌንትራል ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ መስከረም 1992 ዓ. ም.

Adamiak, Richard, Justice and History in The Old Testament: The evalution of divine retribution in the historiographies of the wilderness generation, Cleveland, 1982.

Armstrong, Karen, A History of God, Ballantine Books, New York, 1996.

Engell, Ivan, Studies in Divine Kingship In The Ancient Near East, Oxford, Blackwell, 1967.

Hay, Louise L., You Can Heal Your Life, Hay House Inc., Carland, CA, 1987.

King, Martin Luther JR., I Have A Dream, Hanper, San Francisco, 1992.

Kushner, Harold S., How Good Do We Have To Be?, Little, Brown and Company, New York, 1996.

Kushner, Harold S., Living of Life That Matters, Anchor Books (Random House), Inc. New York, 2002.

Kushner, Harold S. When All You've Ever Wanted Isn't Enough, Sinmon & Schuster, Inc. New York, N.Y. 1986.

Tracy, Thomas F., The God Who Acts: Philosophical and Theological Exploration. Universty Park, PA, 1994.

Tutu, Desmond M., No Future Without Forgiveness, Doubleday, New York, N. Y. 1999.
Volf, Miroslav, Exclusion And Embrace, Abingdon Press, Nashville, 1996.